# 2ኛ ሳሙኤል

## ጥናት አንድ 2ኛ ሳሙ 1፡1-27

የጥናት ዓላማ፡- እውነቱን ተረድቶ አስፈላጊውን እርምጃ እንደወሰደ እንደ ዳዊት፤ እኛም ከሰዎች በሰማነው ነገር ተወስደን ውሳኔ ከማድረግ ይልቅ እውነቱን ለማወቅ የሚያስችሉ ቀጣይ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፤ የተሻለ መረጃ እንዲኖረንና የማንጸጸትበት አይነት እርምጃ ለመውሰድ እንደሚረዳን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "…ወሬውን የነገረውን ወጣት፡ ሳዖልና ልጁ ዮናታን መሞታቸውን እንዴት አወቅህ? ሲል ጠየቀው" 2ሳሙ 1፡5

1. 2ኛ ሳሙኤል 1፡1-27 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ 1 ላይ ስለ ዳዊት ሲናገር "ዳዊት አማሌቃውያንን ድል አድርጎ በመመለስ በጺቅላቅ ሁለት ቀን ቆየ" ይላል። ዳዊት የአገር ንጉስ አልነበረም፤ ታዲያ ለምንድነው በዚህን ጊዜ ከአማሌቃውያን ጋራ መዋጋት የነበረበት? (የዚህን ጥያቄ መልስ ለማግኘት መለስ ብሎ ባለፉት ምዕራፎች የተከናወኑትን ነገሮች መቃኘት ያስፈልጋል)
2. በቁ2-5 ውስጥ ስናይ ይህ ከጦርነት ሥፍራ የመጣው አማሌቃዊ ሰው ዳዊት ዘንድ በደረሰ ጊዜ ከእግሩ ሥር ወድቆ እንደሰገደ እንመለከታለን። ለምን ይመስልሃል ይህ ሰው ለዳዊት የዚህ ዓይነት አክብሮት መስጠት የፈለገው? ይህ ሰው በጦር ሜዳ ላይ የሆነውን ነገር እንጂ እርሱ ራሱ ያደረገውን ነገር አልተናገረም ነበረ፤ ታዲያ ዳዊት የወዳጁን የዮናታንንና የአሳዳጁን የሳዖልን ሞት ማወቅ የቻለው በምን መንገድ ነበረ?
3. ዳዊት ከጦር ሜዳ መጣሁ ያለውን ወጣት "ሳዖልና ልጁ ዮናታን መሞታቸውን በምን አወቅህ?" በማለት ለጠየቀው ጥያቄ በቁ 6-10 ላይ የመለሰውን መልስ በ1ኛ ሳሙ 31፡4-6 ላይ ከሰፈረው የሳዖል አሟሟት ጋራ አነጻጽረን ስንመለከተው የምንረዳው አንድ ነገር ምንድነው? ይህ ሰው ወደ ዳዊት ሲመጣ፤ በተለይም የሳዖልን ዘውድና፣ የክንዱን አምባር ይዞ መምጣቱን ለዳዊት ሲያበስር ምን የጠበቀው ነገር ያለ ይመስልሃል?
4. በቁ11 እና 12 ላይ ዳዊትና ህዝቡ ከጦር ሜዳ የመጣውን ሰው ሪፖርት በሰሙ ጊዜ ያደረጓቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። እነዚህ ከእርሱ ጋራ የነበሩት ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች እንደነበሩና በአንድ ወቅትም እግዚአብሄር ጠላትህን በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃልና እዚሁ ጨርሰው በማለት ስለ ንጉስ ሳዖል መናገራቸውን እናውቃለን። በቁ11-12 የሆነውን ነገር ስናነብ፤ ሰዎቹ ከእርሱ ጋራ ባሳለፉት ጊዜ ውስጥ ዳዊት በህይወታቸውና በአመለካከታቸው ውስጥ ያመጣው ምን ለውጥ ታያለህ? ሰዎች ከአንተ ጋራ በሚያሳልፉት ጊዜ ውስጥ ከህይወትህ መልካም ወይስ ክፉ ይማራሉ?
5. ቁ13-16 ዳዊት ወሬውን ያመጣለትን ሰው የጠየቃቸው ሁለት ጥያቄዎች ምንና ምን የሚሉ ነበሩ? ዳዊት ከጠየቃቸው ሁለት ጥያቄዎች መሃል አንደኛው በዘመናችን በተለይም በቤተ ክርስትያን አካባቢ "የቀባኋቸውን አትዳሱ" የሚል አነጋገር በብዛት ይሰማል፤ ታዲያ ይህ ዳዊት ስለ ሳዖል የተናገረው አባባል በዚህ ዘመን ጥቅሱን ከሚጠቀሱበት አባባል ጋራ ይሄዳል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ።
6. ዳዊት ከማዘን፣ ከመጾምና ልብሱን ከመቅደድ አልፎ ለሳዖልና ለዮናታን ስላደረገው ነገር በቁ17 እና 18 ላይ የምናነበው ምንድነው? ይህ እርሱ የተቀኘው መዝሙር የሳዖልና የዮናታን ስም ከሰው ልብና አዕምሮ ለወደፊትም ተጠብቆ እንዲቆይ ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ሰዎች ስለሌሎች ሰዎች በጎ ህሊና ይዘው እንዲጓዙ ምን ያህል ሙከታ ታደርጋለህ
7. ቁ19-27 ላይ ስንመለከት በተለይም ቁ19 ላይ ብናተኩር፤ ዳዊት ሳዖልን ለህዝቡ ወይም ለእስራኤል ሲያስተዋውቅ ምን በማለት ነው የሚያስተዋውቀው? እነዚህን ቁጥሮች ሁሉ ስንመረምር፤ ዳዊት በጠላትነት ለረጅም ዓመታት በየዋሻው ሲያሳድደው ከከበረው ከሳዖልና፤ እጅግ ከሚወደው ከዮናታን ለማንኛቸው ነው ከመዝሙሩ ሰፋ ያለውን ክፍል የሰጠው?
8. በቁ5 ላይ ወዳለው ሃሳብ ተመልሰን ስንመለከት፤ ዳዊት በዚህ ክፍል ላይ ከጦር ሜዳ ተመለስኩ ያለውን ሰው ተጨማሪ ጥያቄ መጠየቁ ያስገኘለት ነገር ምንድነው? አንተስ ሰው ከሚያመጣልህ ወሬ አልፈህ ምን ያህል እውነቱን ለማወቅ ትመረምራለህ? አብዛኛውን ጊዜ ከሰዎች የምንሰማው ከፊሉን እውነት በመሆኑ፤ ማናቸውንም አይነት እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት ሙሉ እይታ እንዲኖረንና የተሻለ ውሳኔ ማድረግ እንድንችል አስቀድመን እውነትን የሚገልጡ ጥያቄዎች መጠየቅ መልካም ነው።

# ጥናት ሁለት 2ኛ ሳሙ 2፡1-32

የጥናት ዓላማ፡- በተለያየ ምክንያት አስፈላጊ ያልሆነ ጦርነት ውስጥ ገብተን ራሳችንን በምናገኝበት ወቅት፤ እኛ ክርስትያኖችም ሁላችን የአንድ አባት ልጆች መሆናችንን አንዳችን ለሌላችን በማስታወስ ከጥፋት ልንገደብ እንደሚያስፈልገን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "አበኔር ኢዮአብን ጠርቶ…ሰዎችህ ወንድሞቻቸውን ማሳደድን እንዲያቆሙ ትዕዛዝ የማትሰጣቸው እስከ መቼ ድረስ ነው? አለው።" 2ሳሙ 2፡26

1. 2ኛ ሳሙ 2፡1-32 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ ዳዊት ሲያደርግ የምንመለከተው ነገር ምንድነው? ይህ ሰው በእግዚአብሄር እንደተቀባ፣ ቀጣዩ የእስራኤል ንጉስ እርሱ እንደሆነ በማያጠራጥር ሁኔታ ያውቃል፤ ሳዖል መሞቱን ሲያውቅ ተነስቶ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጓዝ ይልቅ ለምንድነው ዳዊት እግዚአብሄርን መጠየቅ ያስፈለገው?
2. ቁ2-7 ላይ፤ በተለይም ቁ2-4 ላይ የሆነውን ስንመለከት፤ ዳዊት ወደ ይሁዳ መሄድ ይኑርበት ወይም አይኑርበት፤ ከይሁዳ ከተሞች ወደ የትኛው መሄድ እንዳለበት ለማወቅ ከእግዚአብሄር ጋራ መመካከሩ፤ በዚህ ክፍል ሲሆን ከምናየው አንጻር መልካም ነገር መሆኑን የምናየው እንዴት ነው? በቁ4-7 ውስጥ ዳዊት የንግሥና ሥፍራውንም ካረጋገጠ በኋላ እንኳን ከልቡ እንዳላወጣው የምንመለከተው ሰው ማን ነው? አንተስ ለሚጠሉህ ወይም በጥላቻ ቀለም ስምህን ለሚቀቡ ሰዎች የዚህ ዓይነት አመለካከት አለህ ወይ?
3. ቁ8-11 በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ከምናነበው፤ ሳዖል ይገዛ የነበረው ግዛት አሁን በስንት ነገስታት ነው የሚተዳደረው? ነገስታቱስ ማንና ማን ይባላሉ? ዳዊት በየዋሻውና በስደት አገር ከመኖር ወጥቶ ዙፋን መያዙን ተመልክተናል፤ ሆኖም በቁ12-16 ላይ የሰፈረውን ታሪክ ስናነብ የንግሥናው ህይወት ዳዊትን የተቀበለው በምን ዓይነት እንደነበረ?
4. በቁ16 ላይ ሊደረግ ላለው ጦርነት የሚካሄድባት ከተማ ስም ማን በመባል ትጠራለች? ይህች ከተማ በተለይም በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ እስራኤል ከአሞራውያን ጋራ ጦርነት በተጋጠሙበት ወቅት እግዚአብሄር ለህዝቡ ተደርጎ የማያውቅ ነገር የተደረገባት ከተማ ነች፤ ይህ በዚያን ጊዜ የተደረገው ተአምራት ምን ነበረ?
5. የኢዮአብና የአቢሳ ወንድም የሆነው አሣሄል የተባለው ሰው በቁ17-23 ላይ ከምናየው ህይወቱን ለማትረፍ ምን ያህል እድል ተሰጥቶታል? በእነዚህ ቁጥሮች በተለይም ቁ22 ላይ ከምናነበው ሃሳብ ተመርኩዘን በአበኔርና በኢዮአብ መካከል ስለነበረው ግንኙነት ምን መገመት እንችላለን?
6. ቁ27-32ትን ላይ በሰፈረው ሃሳብ መሰረት በወንድማማች መሃል ይካሄድ የነበረውን ጦርነት ለማስቆም መደረግ የነበረበት አንድ ነገር ምን ነበረ? ኢዮአብ ወንድማማቾች እንዳይተላለቁ ማድረግ የነበረበትን ነገር አስቀድሞ ባለማድረጉ የተከሰተውና በቁ29-32 ላይ የምናየው ውጤት ምንድነው? በወንድማማች መሃል ያለ አለመግባባት በጊዜው ካልተቀጨና ዝም ከተባለ፤ ቆይቶ በሁሉም ወገን ላይ ጥፋት የሚያስከትል ነገር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።
7. ቁ26 ላይ አበኔር ለኢዮአብ "ሰዎች ወንድሞቻቸውን ማሳደድ እንዲያቆሙ ትዕዛዝ የማትሰጣቸው እስከመቼ ድረስ ነው" በማለት ሲጠይቅ እናያለን። እነዚህ ሰዎች ወንድማማቾች በመባል የተጠሩበት ምክንያት ለምንድነው? የአንድ አባት ልጆች የሆኑ ክርስትያኖች አንዱ ሌላውን ሊያጠፋ ሲያሳድድ ተው አይሆንም ያልክበት ጊዜ አለ ወይ? እኛ ክርስትያኖችም ሁላችን የአንድ አባት ልጆች በመሆናችን አንዱ ሌላውን ሊያጠፋ ሲሞክር ወደ ልባቸው ተመልሰው ጦርነታቸውን እንዲያቆሙ ማድረግ የእያንዳንዳችን ሃላፊነት ነው።

## ጥናት ሶስት 2ኛ ሳሙ 3፡1-39

የጥናት ዓላማ፡- አበኔር የእግዚአብሄር ፈቃድ ምን እንደሆነ ማወቁ ለራሱ መጠቀሚያና ኢያቡስቴን መጉጃ እንጂ ከእግዚአብሄር ጋራ ላለው ግንኙነት እንዳልጠቀመው ሁሉ፤ እኛም የእግዚአብሄርን ፈቃድ መረዳታችንና ቃሉን ማወቃችን ብቻውን በቂ እንደማይሆን፤ ነገር ግን ያወቅነውና የተገለጠልንን የእግዚአብሄር ቃል በመታዘዝ ለበረከት ሊሆንልን እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እግዚአብሄር ለዳዊት በመሃላ የሰጠውን ተስፋ እዳር እንዲደርስ ሳላደርግ ብቀር እግዚአብሄር በአበኔር ላይ ክፉ ያድርግበት፤ ከዚያም የባሰ ያምጣበት።" 2ኛ ሳሙ 3፡9

1. 2ኛ ሳሙ 3፡1-39 በአንድነት ይነቡብ። በቁ1-5 ላይ ስናነብ በዳዊትና በሳዖል መካከል ስለሚካሄደው ጦርነት የሚነግረን ነገር ምንድነው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ዳዊት በኬብሮን በነበረባቸው ሰባት ዓመታት ተኩል ውስጥ ስድስት ወንዶች ልጆች እንደተወለዱለት እናያለን፤ ይህ ማለት በዚያ የተወለዱት የዳዊት ልጆች ቁጥር ስድስት ብቻ ነው ማለት ነው ወይ? አስረዳ። በዚሁ ክፍል ብቻ የምናያቸው ዳዊት ስንት ሚስቶች ነበሩት?
2. አበኔር በሳዖል ልጅ በኢያቡስቴ ላይ እንደተቆጣ በቁ8 ላይ እንመለከታለን፤ በዚህ ቦታ አበኔርን ሊያስቆጣ የቻለው ነገር ምን ነበረ? በቁ8 ላይ አበኔር የሚናገረውን ንግግር ጠለቅ ብለን ስንመረምር፤ እርሱ ከዚህች ሴት ጋራ ዝሙት ማድረጉን ኢያቡስቴ ምንም ነገር መናገር እንዳልነበረበት አድርጎ የሚሰጣቸው ምክንያቶች ምን ምን ነበሩ?
3. በ9-11 ባለው ክፍል ውስጥ አበኔር እግዚአብሄር ለዳዊት ስለገባው ቃል ኪዳን ምን ያህል እውቀት እንዳለው ነው የምንመለከተው? ይህ ሰው በተለይም ይህንን ያህል ስለ እግዚአብሄር የተስፋ ቃል እያወቀ፤ ለምንድነው እስከዛሬ ድረስ ከእግዚአብሄር ሰው ጋራ ከመቆም ይልቅ ከሳዖልና ከእርሱ ሰራዊት ጋራ በመሆን የእግዚአብሄርን ሰው ዳዊትን የሚያሳድደው? አንተስ የራስህ ፍላጎት ከእግዚአብሄር ሃሳብ ይልቅ ሲጎትትህ አግኝተኸው ታውቃለህ ወይ?
4. ቁ12-16 በአንድነት ይነቡብ። በተለይ ቁ12ን ስንመለከት አበኔር በፈጸመው የዝሙት ሃጥያት ንስሃ ከመግባትና ወደ እግዚአብሄር ከመመለስ ይልቅ ምን ሲያደርግ ነው የሚገኘው? አበኔር ከሳዖል ቤት ወጥቶ ወደ ዳዊት ካምፕ ለመቀላቀል የወሰነው ለምን ሃጥያቴ ተነገረኝ ወይም ጥፋቴን ለምን ዝም ብላችሁ አላለፋችሁኝም በሚል እንደሆነ እናያለን፤ ታዲያ ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብና ድርጊት እኛ ባለንበት ዘመን ሲከሰት አይተህ ወይም ሰምተህ ታውቅ ከሆነ ከወገኖች ጋራ ተወያዩበት።
5. በቁ17 ላይ "እግዚአብሄር ለዳዊት፤ በባሪያዬ በዳዊት ህዝቤን እስራኤልን ከፍልስጤማውያን እጅና ከጠላቶቻቸው እጅ እታደጋቸዋለሁ፤ ብሎ ተስፋ ስለሰጠው" በማለት አበኔር የእስራኤል ሽማግሌዎችን ልብ ወደዳዊት ለመመለስ ይናገራል። ይህንን የተስፋ ቃል አበኔር ከተረዳው በህይወቱ መጠቀም የነበረበት መቼ ይመስልሃል? ከላይ በተመለከትናቸው ቁጥሮች ብቻ በመመርኮዝ፤ አበኔር ስለተባለው ሰው ባህርይ ምን ዓይነት ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስችለናል?
6. ቁ25 ትንና ቁ26ትን ስንመለከት፤ ኢዮአብ ስለ አበኔር ማንነትና ባህርይ ለዳዊት የሚነግረው ነገር ምን ነበረ? በቁ22-30 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ስናነብ፤ ኢዮአብ አበኔርን በጦሩ ወግቶ የገደለበት ዋነኛው ምክንያት ለምን ነበረ?
7. ዳዊት በህይወቱ ጠላት ሆኖ ሲያሳድደው የነበረውን የሳዖል ሞት እንዴት እንዳሳዘነውና ሃዘኑንም በተለያየ መንገድ እንደገለጸ ተመልክተናል። ይህ የዳዊት ጠላቶቹን እንኳን እንደ ወዳጅ አድርጎ ማየት በሳዖል ላይ ብቻ የተወሰነ ነገር እንዳልሆነና የዳዊት ባህርይ መሆኑን ቁ31-39 ላይ ያለው ሃሳብ በምን መንገድ ነው የሚያረጋግጥልን?
8. አበኔርን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተለይም በቁ9፣ ቁ10 እና ቁ18 ላይ እንደምናየው አይነት የእግዚአብሄር የተስፋ ቃል እውቀት እያለው ነገር ግን ለሆዱ ሲል ከሳዖል ጋራ መጣበቁ ለእኛ ምን የሚያስተምረን ነገር አለ? አንተስ በምታውቀው የእግዚአብሄር ቃል ትኖርበታለህ ወይስ ለራስህ እንደሚበጅህ መጠቀሚያ ታደርገዋለህ? የእግዚአብሄርን ሃሳብ መረዳትና ፈቃዱ ምን እንደሆነ ማወቃችን ብቻውን በቂ እንደማይሆን፤ ነገር ግን ያወቅነውን ፈቃዱን ለማድረግ የተዘጋጀ ልብ ሊኖረን ያስፈልጋል።

# ጥናት አራት 2ኛ ሳሙ 4፡1-12

የጥናት ዓላማ፡- ከአበኔር የተሰጠው ስልጣን አበኔር ሲሞት አብሮት እንደሄደ ሁሉ፤ ከሰዎች የሚገኝ ሥልጣንም እንዲሁ ሰዎቹ ሲጠፉ አብሮ የሚጠፋ ስለሚሆን፤ እንደ ዳዊት ከእግዚአብሄር ከራሱ የተቀበልነው ስጦታ ከሆነ ግን ሳንደነግጥና ሳንፈራ መኖር እንደሚያስችለን ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “…አበኔር የሳዖልን ልጅ ኢያቡስቴን… በኤፍሬምና በብንያም እንዲሁም በእስራኤል ሁሉ ላይ አነገሰው።” 2ኛ ሳሙ 2፡8-9” “አበኔር በኬብሮን መሞቱን የሳዖል ልጅ ኢያቡስቴ በሰማ ጊዜ ወኔ ከዳው፤ መላው እስራኤልም ደነገጠ።” 2ኛ ሳሙ 4፡1

1. 2ኛ ሳሙ 4፡1-12 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-3 ላይ ስናነብ ኢያቡስቴ ሙሉ በሙሉ ልቡን የጣለበት ወይም ደግሞ ቀኝ እጁ የነበረው ሰው አበኔር ሲሞት የተሰማው ስሜት ምን ነበረ? አበኔር በነበረበት ወቅት ለኢያቡስቴ የወራሪ ጭፍራዎች ቡድን መሪ በመሆን ያገለግሉ የነበሩት ሁለት ሰዎች ስም ማንና ምን ይባል እንደነበረና፤ ተወላጅነታቸውም የት እንደነበረ ተናገር።
2. በቁ4 ላይ ስንመለከት፤ ሜምፊቦስቴ የተባለው የሳኦል የልጅ ልጅ ወይም የዮናታን ልጅ ሁለት እግሮቹ ሽባ እንዲሆኑ ያበቃው ነገር ምን ነበረ? የሜንፊቦስቴ አያትና አባቱ በጦር ሜዳ በሞቱ ሰዓት ይህ ልጅ የስንት ዓመት ልጅ ነበረ?
3. ዳዊት በህይወት ዘመኑ ሁሉ በተለይም የእስራኤል ንጉስ እንዲሆን በእግዚአብሄር ከተቀባ ጀምሮ፤ ይህንን ሁኔታ የሚያውቁ ብዙ ሰዎች ዳዊትን ለዙፋን ለማብቃት የረዱ መስሏቸው የተለያየ ነገር ሲያደርጉ የሚታዩ ሰዎች አይተናል። ለዳዊት ረዳን ብለው በምክርም ሆነ በድርጊት የተስፋ ቃሉን ለማስፈጸም የሞከሩ ሰዎችን አንዳንዶቹን በመዘርዘር ለመናገር ሞክር።
4. በቁ5-8 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ ስንመለከት፤ የብኤሮታዊው የሬሞን ልጆች ሬካብና በዓና የሳዖልን ልጅ ኢያቡስቴን ለመግደል ሲሄዱ ንጉሱ እያደረገ ያለው ነገር ምን ነበረ? እነዚህ ወንድማማቾች የኢያቡስቴን ራስ ቆርጠው ለዳዊት ካመጡለት በኋላ የተናገሩትን ንግግር ስንሰማ፤ ሳዖል ለዳዊት ምኑ እንደሆነ አድርገው ነው ያቀረቡለት?
5. በቁ8 ላይ “እነሆ እግዚአብሄር በዛሬው ቀን ስለ ጌታዬ ስለ ንጉሱ ሳዖልንና ዘሩን ተበቅሏል አሉት።” በሬካብና በዓና አመለካከት እግዚአብሄር የዳዊትን ጠላት ለመበቀል ወይም ለመግደል መሳሪያ አድርጎ የተጠቀመው ማንን ነው? በቁ8 እነዚህ ወንድማማቾች ሊያስታውሱት እየሞከሩ ያሉት በህይወቱ ውስጥ መከራን ያመጣበትን ሰው ሲሆን፣ ዳዊት ግን በቁ9 ላይ ለሰዎቹ ሊያስታውሳቸው የሚሞክረው ነገር ምን ነገር ታያለህ? አንተስ ልብህን የምታደርገው በጠላቶችህ ማንነት ላይ ነው ወይስ በአዳኝ ወይም ጠባቂህ ላይ?
6. ቁ10-12 ላይ ስናነብ ዳዊት የንጉስ ሳዖልን መሞት ዜና ስላመጣለት ሰው በማውሳት ለወንድማማቾቹ ሲናገር፤ ያ ሰው ወሬውን በማምጣቱ ከዳዊት እጅ የተቀበለውን ነገር ምን ብሎ ነው ሲጠራው የምንመለከተው? ከዚህ አነጋገሩ እነዚህ ሁለት ሰዎች ለድርጊታቸው ከዳዊት እጅ ምን ጠብቀው እንደመጡ ነው መረዳት የምንችለው?
7. መለስ ብለን በ2ኛ ሳሙ 2፡8 ላይ ስናነብ የሳዖልን ልጅ ኢያቡስቴን በዙፋን ላይ ያስቀመጠው ማን ነበረ? በቁ4፡1 ላይ ኢያቡስቴ በአበኔር መሞት የተደናገጠው ለምንድነው? እግዚአብሄር ሳይሆን ሰው በስልጥያስቀመጣቸውና ያ ያስቀመጣቸው ሰው ከአጠገባቸው ሲለይ ግራ የተጋቡ ሰዎች ገጥመውህ ያውቃሉ ወይ? ከሰዎች የሚመጣ ሥልጣን ሰዎቹ ሲጠፉ አብሮ የሚጠፋ ሊሆን እንደሚችል፤ ነገር ግን እንደ ዳዊት ከእግዚአብሄር ከራሱ የተቀበልነው ነገር ከሆነ ሳንደነግጥና ሳንፈራ መኖር እንችላለን።

# ጥናት አምስት 2ኛ ሳሙ 5፡1-25

የጥናት ዓላማ፦ ዳዊት የንግስና ሥልጣኑ የእግዚአብሄርን ህዝብ ለማገልገል መሆኑን እንዳወቀ ሁሉ፤ እኛም እግዚአብሄር በቤት ወይም በቤተ ክርስትያን ውስጥ ሃላፊ አድርጎ ሲያስቀምጠን፤ ህዝብን ለማገልገል እንጂ በቅዱሳን ላይ እንድንሰለጥንባቸው እንዳልሆነ ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፦ "በዚያን ጊዜ የጢሮስ ንጉስ ኪራም ወደ ዳዊት መልዕክተኞችን ላከ…እነርሱም ለዳዊት ቤተ መንግስት ሰሩለት። እግዚአብሄር በእስራኤል ላይ ንጉስነቱን እንዳጸናለት፤ ስለ ህዝቡ ስለ እስራኤልም መንግሥቱን እንዳሰፋለት ዳዊት አወቀ።" 2ኛሳሙ 5፡11-12

1. 2ኛ ሳሙ 5፡1-25 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ላይ የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ዳዊት ወዳለበት ወደ ኬብሮን መጥተው ዳዊት በላያቸው እንዲነግሥ ሲጠይቁት፤ ለዳዊት ያቀረቡለት ሁለት ዓይነት ምክንያቶች ምንና ምን ነበሩ? ቁ3 ላይ ስናነብ "እነርሱም ዳዊትን ቀብተው በእስራኤል ላይ አነገሱት።" የሚለው አነጋገር፤ ዳዊት በእግዚአብሄር ቀድሞ የተቀባ አልነበረም ማለት ነው ወይስ ምን ማለት ይመስልሃል?
2. ቁ4-7 ላይ ስናነብ ዳዊትና ህዝቡ ኢያቡሳውያንን ለመውጋት እንደወጡ እንመለከታለን። ከዚህ ቀደም በነበሩት ጊዜአት ዳዊት የህይወቱን አብዛኛውን ጊዜውን ያጠፋው በምን ዓይነት ሁኔዎች ነበረ? ኢያቡሳውያን ለዳዊትና ለሰዎቹ የነበራቸውን ንቀት ለማሳየት የተጠቀሙበት አነጋገር ምን የሚል ነበረ?
3. ቁ6-10 ኢያቡሳውያን በዳዊት ላይ የተናገሩትን የንቀት ንግግር ስንመለከት፤ እነርሱ ሊመለከቱትና ሊረዱት የማይችሉት ዳዊት ብቻ የሚያውቀው አንድ እውነት በዚህ ክፍል ሰፍሮ እናገኘዋለን፤ ይህ ጠላቶቹ ያልተረዱት እውነት ምን ነበረ? ቁ13-16 ላይ ስናነብ ሰለሞን የተወለደው ከብዙ ወንዶች ልጆች በኋላ እንደሆነ እንመለከታለን። ታዲያ ሰለሞን የመጀመሪያ ልጅ አለመሆኑና ሆኖም ግን ዙፋኑን ከንጉሥ ዳዊት መቀበሉ ስለ እግዚአብሄር አሰራር ምን የሚያስተምረን ነገር ይኖራል?
4. ፍልስጤማውያን ብዙ ጊዜ ከእስራኤል ጋራ ጦርነት እንደወጡ እናውቃለን፤ የዚህ ክፍል አቀራረብ ግን እንደምንመለከተው ጦርነታቸው ዛሬ ዒላማ ያደረገው በማን ላይ ነበረ? በዚህ ቁጥር ላይ ፍልስጤማውያን በንጉስ ዳዊት ላይ አወጣጣቸው ከሌላ ጊዜው ለየት የሚል መሆኑን የሚነግረን ክፍል የትኛው ነው? የእግዚአብሄርን ህዝብ ሊመሩ በተሾሙ መሪዎች ላይ ጠላት ያለ የሌለ ሃይሉን አስከትቶ እንደሚነሳ መሪም ሆነ ተመሪ አውቀው በጸሎት መትጋት አስፈላጊ ነው።።
5. በቁ17-19 ውስጥ የሰፈረውን ሃሳብ ስንመለከት፤ ፍልስጤማውያን ለጦርነት መምጣታቸውን በሰማ ጊዜ ዳዊት የወሰዳቸውን ሁለት ዓይነት እርምጃዎች እናነባለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። ዳዊት በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ያደረጋቸው ሁለት ነገሮች አንደኛቸውን ከሌላኛው ልዩ የሚያደርጋቸው ነገር ምን ይታይሃል? እግዚአብሄርን የሚጠይቅበት ነገር ከሆነ፤ ለምንድነው ታዲያ ዳዊት ወደ ምሽጉ መውረድ ያስፈለገው?
6. በቁ18-21 ላይ ስናነብ ፍልስጤማውያን በዳዊት ላይ በሙሉ ሃይላቸው መጥተውበት ድል ተደርገው እንደተመለሱ እናያለን። በቁ22 ላይ ደግሞ የዳዊት ጠላቶች እንደገና ተደራጅተው ለጦርነት ተመልሰው መምጣታቸውን ስንመለከት፤ ከዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ለራሳችን ህይወት መማር የምንችለው ነገረ ምንድነው?
7. ዳዊት ጠላቶቹ በመጡበት በመጀመሪያው ጊዜ የእግዚአብሄርን ፈቃድ እንደጠየቀ ሁሉ፤ ለሁለተኛም ጊዜ ሲመጡ እንደገና የአምላኩን ፈቃድ ሲጠይቅ እናገኘዋለን። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብንገባ ብዙዎቻችን የምንሳሳተው ነገር ምን ይመስልሃል? ዳዊት በጠላቶቹ ላይ መውጣት እንዳለበትና እንደሌለበት እግዚአብሄርን ሲጠይቅ የተሰጠውን መልስ ስትመለከት በሁለቱ መሃል ምን ልዩነት ትመለከታለህ? ከዚህስ ምን መማር የምንችል ይመስልሃል?
8. ቁ11-12ትን መለስ ብለን ስንመለከት፤ ንጉስ ዳዊት እግዚአብሄር መንግሥቱን የማጽናቱና፤ መንግሥቱን የማስፋቱ ምክንያት አድርጎ የተቀበለው ነገር ምን ነበረ? አንተስ በማናቸውም አይነት ሃላፊነት ላይ ብትሆን፤ ከስርህ ላሉ ሰዎች እንጂ ለራስህ ጥቅም እንዳላስቀመጠህ ገብቶሃል ወይ? እግዚአብሄር በተወሰኑ ሰዎች ላይ ሃላፊ አድርጎ ሲያስቀምጠን፤ ከስራችን ያሉትን ሰዎች ለማገልገል የሚጠቀምብን መሳሪያዎች እንጂ በእግዚአብሄር ህዝብ ላይ እንድንሰለጥን እንዳልሆነ ሊገባን ያስፈልጋል። 2ኛ ቆሮ 10፡8

# ጥናት ስድስት 2ኛ ሳሙ 6፡1-23

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ዋነኛ ሃሳብ ታቦቱ የአቢዳራን ቤት እንዲባርክ ብቻ ሳይሆን ለእስራኤል ሁሉ በረከት እንደሆነ ሁሉ፤ በእኛ ውስጥ ያለው ኢየሱስም በውስጣችን ይዘነው እንድንባረክበት ብቻ ሳይሆን፤ ከእኛ አልፎ ለአካባቢያችን በረከት እንዲሆን የእግዚአብሄር ሃሳብ ስለሆነ፤ ወደ ዓለም ሁሉ ይዘነው መውጣት እንዳለብን ለማሳሰብ ነው።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “በዚህ ጊዜ በእግዚአብሄር ታቦት ምክንያት የአቢዳራን ቤተሰብና ያለውን ሁሉ እግዚአብሄር ባረከለት ብለው ለዳዊት ነገሩት፤ ስለዚህ ዳዊት ወደዚያው ወርዶ የእግዚአብሄርን ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ በታላቅ ደስታ አመጣው” 2ኛ ሳሙ 6፡12

1. 2ኛ ሳሙ 6፡1-23 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-5 ላይ ስናነብ የእግዚአብሄርን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት በተደረገው ሥነ ሥርዓት ላይ የተሳተፉት እነማን እንደነበሩ ተናገር። ይህንን የሚያህል ብዛት ያለው ህዝብ የእግዚአብሄርን ታቦት ከማጀብ ሌላ በተጨማሪ ሲያደርግ የምንመለከተው ነገር ምንድነው?
2. ቀደም ብለን ባነበብነው በቁ5 ላይ የታየውን የሽብሸባና የዝማሬ መንፈስ ወደ ሃዘን እንዲቀየር ያደረገው በቁ6-8 የምናየው ነገር ምን ነበረ? “የእግዚአብሄር ቁጣ ዖዛን ስለሰበረው ዳዊት ተከፋ፣ አዘነም” በማለት ቁ8 ይነግረናል። ዳዊት በህይወቱ ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች በእግዚአብሄርን እጅ ሲሞቱ ሳይመለከትና ሳይሰማ እንደማይቀር እናውቃለን፤ ታዲያ ለምን ይመስልሃል በዖዛ ላይ የሆነው ነገር ልቡን ያሳዘነው?
3. በቁ8 ላይ የዖዛ በእግዚአብሄር ተቀስፎ መሞቱ በዳዊት ህይወት ውስጥ ሃዘንና መከፋትን እንዳስከተለ ተመልክተናል። ቁ9-11ድን ደግሞ ወረድ ብለን ስናነብ ይህ ሁኔታ በዳዊት ውስጥ የፈጠረው ሌላ ስሜትም እንደነበረ እንመለከታለን፤ ይህ ስሜት ምን እንደነበረ ተናገር። ዳዊት ከተሰማው ስሜት ተነስቶ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? ዳዊት በወሰነው ውሳኔ ሲጠቀም የምናየው ሰው ማን ነው? አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሄርን ነገር እሺ ብለን በማስተናገዳችን ብቻ በረከቱን ወደ ቤታችን የምናስገባበት መንገድ ሊሆንልን ይችላል።
4. በእግዚአብሄር ታቦት ምክንያት የአቢዳራ ቤት እንደተባረከና ሰዎችም ሄደው ለዳዊት ይህንኑ ነገር እንደነገሩት ቁ12 ይነግረናል። ከታቦቱ የተነሳ በአቢዳራ ቤት የመጣውን የእግዚአብሄር በረከት ለዳዊት የነገሩት ሰዎች ራሳቸው ይህንን ሁኔታ እንዴት ሊያውቁ የቻሉ ይመስልሃል?
5. ምዕራፍ ስድስትን በአጠቃላይ ስንመለከት፤ ንጉስ ዳዊት የእግዚአብሄር ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ለማጓጓዝ ሁለት ጊዜ ሙከራ እንዳደረገ እንመለከታለን። በዳዊት የመጀመሪያ ሙከራና፤ በሁለተኛ ሙከራው መሃል የምታያቸውን ተመሳሳይነቶች፤ እንዲሁም ደግሞ በሁለቱ ሙከራዎች መሃል የሚታዩህን ልዩነቶች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር።
6. የዳዊት ሚስት ሚልኮልን በቁ16-19 ባለው ክፍል ውስጥ ስንመለከታት ሕዝቡ ሁሉ የእግዚአብሄርን ታቦት በታላቅ ደስታና ሽብሸባ ሊያመጣ በሄደበት ሰዓት እሷ የምትገኘው የት ነበረ? ከህዝቡ ጋራ ታቦቱን ለማምጣት ባለቤቷን ተከትላ አለመሄዷንና፤ ስለ ንጉስ ዳዊት የተናገረችውን የስንፍና ንግግር በአንድነት ስንመለከት፤ ሰለ ሚልኮል መንፈሳዊ ህይወት ሁኔታ ምን ይነግረናል?
7. ቁ18ትንና ቁ20ን ስናነብ፤ ዳዊት በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሲባርክና ሲመርቅ የምናገኘው ሁለት ዓይነት ሰዎች እነማን ናቸው? የዳዊትን ምርቃት ለመቀበል ዝግጁ ያልነበረው የትኛው ክፍል ነበረ? አንተስ ከራሷ አልፋ የቤተሰቧን በሙሉ በረከት እንደዘጋችው እንደ ሚልኮል የሌሎችን በረከት የምትዘጋ ነህ ወይስ የበረከት ምክንያት የምትሆን ነህ?
8. በቁ20 ላይ ሚልኮል ራቁቱን ሲጨፍር እንደነበረ አድርጋ ስትናገር ነው የምንመለከታት፤ ሆኖም በቁ14 ላይ ስንመለከት ግን ዳዊት ካህናቱ የሚለብሱትን ኤፉድ ለብሶ እንደነበረ እናያለን። ለሚልኮል በእግዚአብሄር ዘንድ የከበረው ልብስ እንደምን ሆኖ ነው የታያት?
9. ቁ12ትን ስናነብ ታቦቱ ከአቢዳራ ቤት ወጥቶ ወደ የት ሲወሰድ ነው የምናየው? በታቦቱ ምክንያት አቢዳራና ቤተሰቡ ሁሉ እየተባረከ መሆኑን እያየ ለምንድነው ዳዊት የእግዚአብሄርን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም መውሰድ የወሰነው? የእግዚአብሄር ፈቃድ አንተ በኢየሱስ በኩል ያገኘኸው በረከት ለሌሎች ሁሉ እንዲደርስ እንደሆነ ተረድተሃል ወይ? እኛ ክርስቶስ በውስጣችን መግባቱና ህይወታችንን መባረኩ መልካም ቢሆንም፤ እግዚአብሄር ግን በረከቱ ከእኛ አልፎ ብዙዎችን እንዲነካ መፈለጉን ማስታወስ ያስፈልገናል።

# ጥናት ሰባት 2ኛ ሳሙ 7፡1-29

የጥናት ዓላማ፡- ሃሳቦች ከቀን ልብ መምጣታቸው፣ መልካም ሃሳብ መሆናቸውና፣ በሰው አመለካከት ስሜት የሚሰጡ መሆናቸው ብቻ በቂ እንዳልሆነ፤ ነገር ግን አስቀድመን የእግዚአብሄር ፈቃድ ምን እንደሆነ ማወቅና ግልጽ አድርጎ የነገረን ነገር ካለ ደግሞ ለዚያ ቅድሚ መስጠት እንደሚኖርበን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ናታንም እግዚአብሄር ከአንተ ጋራ ስለሆነ ያሰብከውን ሁሉ አድርግ አለው። በዚያች ሌሊት የእግዚአብሄር ቃል እንዲህ ሲል ወደ ናታን መጣ፤ ሂድና ባሪያዬን ዳዊትን… የምኖርበትን ቤት የምትሰራልኝ አንተ አይደለህም ” 2ኛ ሳሙ 7፡3-5

1. 2ኛ ሳሙ 7፡1-29 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-3 ላይ ንጉሱ ዳዊት ራሱ የሚኖርበትን ሁኔታና የእግዚአብሄር ታቦት ያለበትን ሁኔታ አነጻጽሮ ለመመልከት እድል የሰጠው ነገር ምንድነው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ዳዊት እያወዳደረ የሚናገራቸው ሁለቱ ሃሳቦች ምንና ምንድናቸው? ከዚህ አነጋገሩና አስተሳሰቡ ስለዳዊት ልብ ምን ማየት ይቻላል? አንተስ በእግዚአብሄር ቤት የሚጎድለውና በአንተ ሊሞላ የሚችለውን ነገር ለማሰብ ጊዜ ትወስዳለህ ወይ?
2. ቁ5-7ትን ስናነብ ዳዊት በልቡ ላሰበውና ለነብዩ ለነገረው ሃሳብ የእግዚአብሄር ምላሽ ምን እንደነበረ ተመልክተናል። ከቁ8 እና በቁ9 ላይ ደግሞ እግዚአብሄር ለዳዊት ከዚህ በፊት ያደረገለትን ነገሮች ይዘረዝርለታል፤ እነዚህ ለዳዊት የተደረጉለት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። ከቁ10-16 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር የዘረዘራቸው ነገሮች በቁ8-9 ውስጥ ከተዘረዘሩት ነገሮች የሚለዩበት ነገር ምንድነው?
3. እግዚአብሄር ለዳዊት ብዙ እንዳደረገለት ከክፍሉ ተረድተናል። ለዳዊት ከዚህ በፊት የተደረገውንና፣ ገና እግዚአብሄር ሊያደርግለት ቃል የገባውን ስንመለከት የትኛው ይበልጣል ትላለህ? በቁ10-16 ውስጥ ዳዊት ለእግዚአብሄር ሊያደርግ ያሰበውን እቅድ፣ እግዚአብሄር አዞሮ እርሱ ራሱ ለዳዊት እንደሚያደርገው የተናገረው አንድ ነገር ምንድነው?
4. 2ኛ ሳሙ 7፡14ትንና፣ ዕብ 12፡7-8ትን ስንመለከት በአባትና ልጅ መሃል ስላለው ግንኙነት የምትማራቸውን ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ተናገር። ዳዊት በነብዩ በናታን በኩል እግዚአብሄር ይህንን ሰፊና የረጅም ጊዜ ዕቅድን ሁሉ ያዘለ ሃሳብ በነገረው ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ ያደረገው ነገር ምን ነበረ? አንተስ አንድ መልካም የሆነ ነገር ሲገጥምህ በመጀመሪያ የምትሄደው ወደ ማን ነው?
5. ቁ18 ላይ “ከዚያም ንጉስ ዳዊት ገባ፤ በእግዚአብሄር ፊት ተቀምጦ እንዲህ አለ…” ይላል። ጸሎትን አስመልክቶ ይህ ክፍል ሊያስተምረን የሚችለው አንድ እውነት ምን ይታይሃል? በቁ19 ላይ ንጉስ ዳዊት ሲጸልይ የተናገረውን ነገር ስታነብ ምን ለማለት እንደፈለገ ነው የምትረዳው?
6. እግዚአብሄር ለዳዊት ሊያደርግለት ስላለው ስለወደፊቱ ነገር በቁ21 ላይ ስናነብ ዳዊት በእምነት የተቀበለው መሆኑን የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው? ቁ22-24 ላይ ስንመለከት ዳዊት ከሌሎች ጋራ በማወዳደር የበላይ አድርጎ የሚናገርላቸው ሁለቱ ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
7. ቁ27 ላይ ዳዊት ጸሎት ለማድረግ ድፍረት የሆነለትን ነገር ለእግዚአብሄር ሲናገር እናየዋለን፤ በዚህ ቁጥር ላይ ለዳዊት የጸሎት ድፍረት የሰጠው ነገር ምን ነበረ? አንተስ እግዚአብሄር የሰጠውን የተስፋ ቃል ተመርኩዘህ ስትጸልይ ምን ያህል ድፍረት ይሰጥሃል? ዕብ 13፡5-6
8. በቁ3 ላይ ነብዩ ናታን ዳዊት ላነሳው ሃሳብ የሰጠው ምላሽ ምን የሚል ነበረ? ቁ5 ላይ ደግሞ ዳዊት ላመጣው ሃሳብ እግዚአብሄር ፈቃዱ ምን እንደሆነ ያስታወቀው ምን በማለት ነው? አንድ ሃሳብ መልካምና ቅንነት የተሞላበት በመሆኑ ብቻ እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ አድርገህ የወሰድከበት ጊዜ ትዝ ይልሃል ወይ? አንድ ሃሳብ መልካምና ቅንነት የተሞላበት መሆኑ ብቻ የእግዚአብሄርን ፈቃድ የሚያረጋግጥ እንዳልሆነ፤ ስለዚህም ሁልጊዜ እግዚአብሄር የራሱን ሃሳብ እንዲናገር ለእርሱ ቅድሚያ መስጠት ተገቢ ነው።

# ጥናት ስምንት 2ኛ ሳሙ 8፡1-18

የጥናት ዓላማ፡- ዳዊት ሊጠቀምባቸው የሚችላቸውን ፈረሶች በአምላኩ እንዳይታመን ልቡን እንዳይሰቡት ቋንጃቸውን እንደቆረጠ ሁሉ፤ እኛም በእግዚአብሄር እንዳንታመንና እርሱን ብቻ መከታ እንዳናደርግ በእኛና በአምላካችን መሃል የሚገባውን ማንኛውንም ነገር፤ ምንም ያህል ዋጋን የሚያስከፍለንም እንኳን ቢሆን ከህይወታችን አውጥተን መጣል እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ዳዊትም አንድ ሺህ ሰረገሎች፣ ሰባት ሺህ ፈረሶችና፣ ሃያ ሺህ እግረኞች ማረከበት። ቁጥራቸው መቶ የሆነ የሰረገላ ፈረሶች ብቻ ሲቀሩ ሌሎቹን በሙሉ ቋንጃቸውን ቆረጠ።" 2ኛ ሳሙ 8፡4

1. 2ኛ ሳሙ 8፡1-18 በአንድነት ይነበብ። በቁ6 ላይ "እግዚአብሄርም ዳዊት በሄደበት ሁሉ ድልን ሰጠው" በማለት ጸሐፊው የሚናገረውንና፤ በ2ኛ ሳሙ 3፡18 እግዚአብሄር ስለ ዳዊት ከተናገረው ሃሳብ ጋራ አጣምረን ስንመለከት "በሄደበት ሁሉ" የሚለው አነጋገር፤ ዳዊት ወደፈለገበት ሄዶ የፈለገውን ሊያደርግ ሲነሳ እግዚአብሄር ድል ይሰጠዋል ማለት ነው ወይስ ይህ ሃሳብ ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ።
2. በ2ኛ ሳሙ 7፡11 ላይ "እንዲሁም ከጠላቶችህ ሁሉ እጠብቅሃለሁ።" በማለት እግዚአብሄር የተስፋ ቃልን ሰጥቶታል፤ ዳዊት ግን በምዕራፍ 8 ውስጥ ስንመለከት በዙሪያው የነበሩትን ጠላቶቻቸውን ሁሉ አንድ በአንድ ሲያጠፋ እንመለከታለን። እግዚአብሄር ጠላቶቹን እንደሚያጠፋለት የተሰፋ ቃል ሰጥቶት እያለ ዳዊት ተነስቶ ይህን ማድረጉ የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?
3. ምዕራፍ ስምንትን ስናነብ የተካሄዱት ጦርነቶች ሁሉ በአንድ ወር ወይም በአንድ አመት ውስጥ ብቻ የተከናወኑ እንዳልሆኑ መረዳት አያዳግትም። ይህንን ሁሉ ስንመለከት ዳዊት አብዛኛው ዘመኑ ማንን በማሳደድና በማጥፋት ላይ ያተኮረ ነበረ ማለት እንችላለን? በአንጻሩ ደግሞ ከእርሱ በፊት የነበረውን የእስራኤል ንጉስ ሳኦልን ስንመለከት፤ የዚህ ሰው አብዛኛው የንግሥና ዘመን የባከነው ምን በማደረግ ነበረ ማለት ይቻላል? አንተስ ዘመንህን የምታጠፋው ጠላትህን በማሳደድ ይሆን ወይስ ወንድምህን?
4. ቁ11 "ንጉስ ዳዊትም ቀድሞ ካስገበራቸው መንግሥታት ሁሉ በገባለት ብርና ወርቅ እንዳደረገው እነዚህንም ኢቃዎች ለእግዚአብሄር ቀደሳቸው።" ዳዊት በዚህ ምዕራፍ ላይ ባደረጋቸው ጦርነቶች የተገኘውን ምርኮ ሁሉ ለእግዚአብሄር እንደቀደሳቸው እናያለን፤ ዳዊት ይህንን ማድረጉ ምን ማለቱ ይመስልሃል? ቁ9 እና 10ርን ስናነብ ዳዊት ለእግዚአብሄር የለየው በጦርነት ያሸነፈውን ብቻ ሳይሆን በስጦታ መልክ የመጣለትንም ብርና ወርቅ ለእግዚአብሄር እንደለየ እናያለን፤ እሺ በጦርነት የተገኘውስ እሺ፤ ለራሱ እንዲሆን የተሰጠውን ስጦታስ ዳዊት ለምን ለእግዚአብሄር ይሰጣል?
5. ቁ13 ላይ "ዳዊት የጨው ሸለቆ በተባለው ሥፍራ አስራ ስምንት ሺህ ኤዶማውያንን ገድሎ ከተመለሰ በኋላ ስሙ ገነነ።" የሚለውን ሃሳብ ስናነብ፤ እግዚአብሄር 2ኛ ሳሙ 7፡9-16 ላይ ወደፊት በዳዊት ህይወት ሊያደርግ ያለውን ነገሮች የተስፋ ቃል በገባ ሰዓት ከተናገራቸው ነገሮች መሃል ተፈጻሚነት ማግኘት የጀመረው የትኛው ሃሳብ ነው ትላለህ?
6. በቁ15-18 ላይ ስንመለከት፤ ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ እንደነገሰ ደግሞም ፍትህና ርትዕን እንዳሰፈነ እናነባለን። በተለይም በቁ15 ላይ በማተኮር፤ ይህ ዳዊት ያሰፈነው ፍትህና ርትዕ ብዙ የአገር አስተዳዳሪዎችና እንዲሁም ብዙ የአገር ነገሥታት ማድረግ የሚሳናቸው አንድ እጅግ በጣም አስፈላጊና በእግዚአብሄርም አይን ትልቅ ሥፍራ የሚሰጠው ነጥብ በዚህ ክፍል ተጠቅሷል፤ ይህ ነጥብ ምን እንደሆነ ተጋ ብለህ በማሰብ ለመናገር ሞክር።
7. ቁ4 ላይ ዳዊት ብዙ ሰረገሎችና ፈረሰኞችን እንደማረከ፤ ከማረካቸውም ውስጥ አንድ መቶ ብቻ በማስቀረት የተቀሩትን ፈረሶች በሙሉ ቋንጃቸውን እንደቆረጠ እናያለን። በተለይም በዳዊት ዘመን ፈረሶች ለጦርነት እጅግ አስፈላጊ የሆኑ እንስሶች እንደሆኑ  እያወቀ፤ ታዲያ ለምን ይመስልሃል ዳዊት ይህንን ነገር ለማደረግ የወሰነው? አንተስ እምነትህን ሊሸረሽሩ የሚችሉ ከጎንህ ያስቀመጥካቸው ነገሮች አሉህ ወይ? ልባችንን ከእግዚአብሄር ላይ አንስተን ትምክህታችንን በሌላ ነገር እንድናደርግ ፈተና ውስጥ የሚጨምሩንን ነገሮች ዋጋ ቢያስከፍሉንም ከህይወታችን አውጥተን መጣል ይኖርብናል።

# ጥናት ዘጠኝ 2ኛ ሳሙ 9፡1-13

የጥናት ዓላማ:- ዳዊት ለሜምፊቦስቴ ያሳየው ቸርነት ከራሱ የመነጨ እንዳልሆነ እንደተረዳ ሁሉ፤ እኛም ማናቸውንም ዓይነት መልካም ነገር ብናደርግ፤ ያንን ማድረግ ያስቻለን በውስጣችን የሚሰራው የእግዚአብሄር መንፈስ እንጂ ከራሳችን ማንነት የሚመነጭ እንዳልሆነ ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ:-”ንጉሱም የእግዚአብሄርን ቸርነት እንዳደርግለት ከሳዖል ቤት የቀረ ሰው የለምን? ብሎ ጠየቀው።” 2ኛ ጢሞ 9፡2

1. 2ኛ ሳሙ 9፡1-13 በአንድነት ይነበብ። በዘመናት ሁሉ አገራችንንም ጨምሮ፤ ዛሬ የተነሳው ገገር ቀድሞ በነበረው አገዛዝ ውስጥ ለተሳተፉት ግለሰቦች ላይ ሊያደርግ የሚሸርበው ነገር ምንድነው? በቁ1 ላይስ ንጉስ ዳዊት ለቀደመው ንጉስ የሳዖል ቤተሰብ ለሆነ ሰው ሊያደርግ የተነሳሳው ነገር ምንድነው? ለምንድነው ዳዊት በተለይም ሳዖል በህይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ ተቀናቃኙ እንደነበረ እያወቀ የእርሱን ቤተሰቦች በመፍራት እነርሱን ወደማጥፋት አስተሳሰብ ያልሄደው?
2. በቁ1-3 ላይ ስናነብ፤ ዳዊት ለጠየቀው ጥያቄ መልስ አድርገው ያቀረቡለት ሰው ማን ነበረ? በተለይም በሰው ዓይን ስንመለከት ይህንን የተገኘውን ሰው የበለጠ ቸርነት የሚያስፈልገው ሆኖ የሚታይበት ምክንያት ለምንድነው?
3. ንጉሥ ዳዊት ሲባን ሲጠይቀው “የእግዚአብሄርን ቸርነት የማደርግለት ሰው” አለው እንጂ ስለ ሰውየው ቁመና፣ ስለ ሰውየው መልክ፣ ስለ ሰውየው ችሎታ ወይም ደግሞ ሰውየው ስላለው ነገር ሲጠቅስ አናይም፤ ታዲያ ለምንድነው ሲባ ስለ ዮናታን ልጅ የእግር ሽባነት መናገር የፈለገው? ሜምፊቦስቴ በንጉስ ዳዊት ተፈልጎ ሲገኝ የራሱ የሆነ የመኖሪያ ቤት እንኳን እንዳልነበረው እናያለን፤ ታዲያ ይህ ሰው በዳዊት ተጠርቶ እስኪሄድ ድረስ የት ነበረ ይኖር የነበረው?
4. ቁ6 ላይ የሳዖል የልጅ ልጅ የሆነው ሜምፊቦስቴ በዳዊት ፊት በቀረበ ጊዜ ለጥ ብሎ እጅ እንደነሳ እናነባለን፤ በዚህን ሰዓት እያቱ ሳዖል ዳዊትን ያደረገውን ሁሉ የተረዳው ሰው ወደ ዳዊት ተጠርቶ ሲሄድ ምን ዓይነት ሃሳብ በጭንቅላቱ የሚመጣ ይመስልሃል? በቁ7 ላይ ዳዊት ምናልባትም የሜምፊቦስቴን ሁኔታ ተመልክቶ ሳይሆን አይቀርም፤ በመጀመሪያ ለዚህ ሰው የተናገረው አንድ ነገር ምን ነበረ? ምንም እንኳን የማይገባን ብንሆንም እኛንም እግዚአብሄር ወደ ራሱ በማስጠጋት አይዟችሁ አትፍሩ የሚለን አምላክ ነው ያለን።
5. በቁ7 ላይ ዳዊት ለዮናታ እንደሚያደርግለት ቃል የገባቸው ቢያንስ ሁለት ነገሮችን እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እነዚህን ክፍሎች ስንመለከት ሜምፊቦስቴ ይህንን ሁሉ ነገር ለማግኘት ምንም ነገር ሲያደርግ አናይም፤ ታዲያ ዳዊት በምን ምክንያት ነው ለሜምፊቦስቴ ይህንን ሁሉ ነገር ለማድረግ የወሰነው? እኛም ብንሆን ከእግዚአብሄር የተቀበልነው ቸርነት ሁሉ ከማንነታችን የተነሳ ሳይሆን ካፈቀረን ከልጁ የተነሳ መሆኑን መዘንጋት አይገባንም።
6. በቁ8 ላይ ሜምፊቦስቴ የተደረገለት ነገር ከአዕምሮው በላይ ሆኖበት “…ለእኔ ይህንን ያህል የምታደርግልኝ አገልጋይህ ኧረ ማን ነኝ?” በማለት ዳዊትን ሲጠይቅ እንመለከታለን፤ ዳዊት በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የገባበትና ከሜምፊቦስቴ ተመሳሳይ አይነት አነጋገር የተናገረበት ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የምታስታውሰው ነገር ካለ ተናገር። ጠቅላላ ምዕራፍ 9ን ስንመለከት ዳዊት በመልዕክተኛ ሳይሆን አብዛኛውን እርሱ ራሱ ለሜምፊቦስቴም ሆነ ለሲባ ቀጥተኛ የሆነ ትዕዛዝ ሲሰጥ እናያለን፤ ይህ ድርጊቱ ምን ያሳየናል?
7. ሜምፊቦስቴ የሰው ቤት ጥገኛ ሆኖ ከመኖር ህይወት ወጥቶ በ2ኛ ሳሙ 10-13 ስንመለከት ብዙ አገልጋዮች የሚታዘዙለት ሰው እንደሆነ እንመለከታለን፤ እነዚህን ቁጥሮች ስናነብ ሜምፊቦስቴ ቢያንስ ስንት የሚያገለግሉት ሰዎች አሉ ብለህ ትገምታለህ? የሳዖል የልጅ ልጅ የሆነው ሜምፊቦስቴ በዳዊት እጅ መገደል ሲገባው፤ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ግን ሲደረግለት የምናየው ጥንቃቄ እንደ ምን ዓይነት ሆኖ ነው የምናየው? አንተስ ሞት የሚገባህ እንደነበርክና ዛሬ ግን ለእግዚአብሄር እንደ ልጅ ሆነህ መቆጠርህ ምን ያህል የምትደነቅበት ነገር ሆኖልህ ይሆን?
8. በቁ3 ላይ የምንመለከተውና ንጉሥ ዳዊት ለሰዎቹ ያቀረበላቸውን “የእግዚአብሄርን ቸርነት እንዳደርግለት ከሳዖል ቤት የቀረ ሰው የለምን” የሚለው ጥያቄ፤ ዳዊት የቸርነት ምንጩ ከእርሱ እንዳልሆነ መረዳቱን የሚጠቁመን የትኛው ሃሳብ ነው? ማድረግ የቻልካቸው መልካም ነገሮች ሁሉ ምንጫቸው ከእግዚአብሄር እንደሆነ ተገንዝበሃል ወይ? እኛ ምንም ዓይነት መልካም ነገር ብናደርግ፤ ያንን ማድረግ ያስቻለን በውስጣችን የሚሰራው እግዚአብሄር እንጂ ከራሳችን ማንነት የሚመነጭ እንዳልሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል።

# ጥናት አሥር 2ኛ ሳሙ 10፡1-19

የጥናት ዓላማ፡- ምንም እንኳን እያንዳንዳችን በተለያየ ሥፍራና በተለያየ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ተሰልፈን ጠላትን የምንዋጋ ብንሆንም፤ ሁላችንም የአንድ መንግሥት ሰራዊት ስለሆንን፤ የራሳችንን ማሸነፍ ብቻ ሳንመለከት፤ ሌላው ወንድማችን በጠላት ሲጠቃና ሲሸነፍ ስናይ በሚያስፈልገው ሁሉ ለመርዳት ዝግጁ መሆን እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ኢዮአብም እንዲህ አለ፤ ሶርያውያን የሚያይሉብኝ ከሆነ አንተ መጥተህ ትረዳኛለህ፤ አሞናዊያን የሚያይሉብህ ከሆነ እኔ መጠቼ እረዳሃለሁ። እንግዲህ በርታ፤ ለህዝባችንና ለአምላካችን ከተሞች በጀግንነት እንዋጋ።” 2ኛ ሳሙ 10፡11-12

1. 2ኛ ሳሙ 10፡1-19 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ላይ ስንመለከት፤ ንጉስ ዳዊት ለአሞናውያን ንጉስ ለሐኖን ሊያደርግ ያቀደውና ያደረገው ነገር ምን ነበረ? አዲስ የነገሰው የአሞናውያን ንጉስ፤ ዳዊት የላካቸውን ሰዎች መልዕክታቸው ምን እንደሆነ ከመስማቱ አስቀድሞ ስለእነርሱ የሰማው ከማን አፍ ነበረ?
2. የአሞናውያን መኳንንት የዳዊት መልዕክተኞች ስለመጡበት ምክንያት ለጌታቸው ለሐኖን ምን አይነት መረጃ ሲሰጡ ነው የምንመለከተው? ይህ አዲስ የነገሰው ንጉስ መውሰድ ያለበትን እርምጃ ለመወሰን መኳንንቱ የሰጡትን መረጃ እውነት ይሁን ወይም ውሸት ለመረዳትምን ያህል ጥረት እንዳደረገ ነው የምናየው? ሰዎች በነገሩን ነገር ተመርተን፤ ሁኔታውን ሳናጣራና ከሚመለከተው ሰው ሳንሰማ እርምጃ ለመውሰድ ከመቸኮል መቆጠብ ያስፈልገናል።
3. በቁ4-8 ላይ ከምንመለከተው የአሞራዊያን ንጉስ ወደ ሃገሩ ተልከው በመጡት በዳዊት መልዕክተኞች ላይ ያደረገባቸው ነገር ምን እንደነበረና፤ ዳዊት ደግሞ ይህንን ሁኔታ በሰማ ጊዜ የወሰደው እርምጃ ምን እንደነበረ ተናገር። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስናነብ፤ የዳዊትን ቅን የሆነ አስተሳሰብ በማጣመም መኳንንቱ በንጉስ ሐናን ጆሮ ውስጥ የተሳሳተን ነገር ሹክ በማለታቸው ምክንያት ሁለቱን ወዳጆች ሊሆኑ የሚችሉትን ነገስታት ወደ ምን ደረጃ ላይ ሲያመጣቸው ነው የምንመለከተው?
4. በቁ9-10 ላይ ኢዮአብና ወንድሙ አቢሳ አሰላለፋቸውን ስንመለከት፤ የኢዮአብ ሰራዊት ሊዋጋ የተዘጋጀው ከእነማን ጋራ ነው? ወንድሙ አቢሳስ እንዲዋጋ የተመደበው ከየትኛው ሰራዊት ጋራ ነው? እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች በአንድ ላይ ሆነው ጠላታቸውን እንዳይዋጉ የሆኑበትና በሁለት አቅጣጫ መሰለፍ ያስፈለጋቸው በምን ምክንያት ነው?
5. የንጉስ ዳዊት የጦር መሪ የሆነው ኢዮአብ በቁ12 ላይ ለወንድሙ ለአቢሳ ምን በማለት ነው ሲያበረታታው የምንመለከተው? ይህንኑ ቁጥር ትኩርት ሰጥተን ስናነበው፤ በዚህ ጦርነት ውስጥ የኢዮአብና የአቢሳ ሃላፊነት ምን እንደሆነና፤ የአምላካቸው የእግዚአብሄር ሃላፊነት ደግሞ ምን እንደሆነ አስፍሮታል። የሰውና የእግዚአብሄር ሃላፊነት በማለት መለየት የምንችላቸውን ነገሮች በቁ12 ኢዮአብ ከተናገረው በመለየት አስረዳ።
6. ቁ13 19 ላይ የሰፈረውን እስራኤል ከጠላቶቻቸው ከአሞናውያንና ከሶርያውያን ጋራ ያካሄዱትን ጦርነት ስንመለከት ድል ያደረገው ማን ነበረ? የእስራኤል ጠላቶች መሸነፋቸውን ባወቁ ጊዜ በተለይም በቁ15 ላይ ስናነብ፤ እነዚህ የእስራኤል ጠላቶች ሲያደርጉ የምንመለከተው ነገር ምንድነው? ጠላታችን አንዴ ብቻ አሸንፈነው ተስፋ የሚቆርጥና ዳግም ተመልሶ እንደማይመጣ ማሰብ አድርገን ማሰብ ሞኝነት ነው።።
7. ወንድማማቾቹ ኢዮአብና አቢሳ ለአንድ መንግሥት የቆሙ ሰዎች ወታደሮች ናቸው፤ የእያንዳንዳቸው ተልዕኮ የራሳቸውን ጠላት ማሸነፍ ብቻ እንዳልሆነ ማወቅ የምንችለው እንዴት ነው? ከራስህ አልፈህ በዙሪያህ ከጠላት ጋራ እየተፋለሙ ያሉትን ወንድሞችህን ለማገዝ ሞክረህ ታውቃለህ? የአንድ መንግሥት ሰራዊት እስከሆንን ድረስ፤ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ቤተ ክርስትያን፤ የራሳችንን ጦርነት ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን፤ ከጎናችን ያሉትን ወንድም እህቶቻችን ድልን እስኪቀዳጁ ድረስ ከጎናቸው ሆነን መዋጋት ይኖርብናል።

# ጥናት አሥራ አንድ 2ኛ ሳሙ 11፡1-27

የጥናት ዓላማ፡- በእግዚአብሄር እንደልቤ የተባለው ዳዊት እንኳን ሐጥያት ትክክለኛ እይታ እንዳይኖረው ዓይኑን እንዳሳወረው ሁሉ፤ ማናችንንም ቢሆን ሐጥያት በህልማችን እንኳን እናደርገዋለን ብለን የማንገምተውን ሊያስደርገን የሚችል ሃይል እንዳለው፤ ስለዚህም ሳንዘናጋ ዘወትር በተጠንቀቅና በእግዚአብሄር ፍርሃት መኖር እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሲነጋም ዳዊት ለኢዮአብ ደብዳቤ ጽፎ በኦርዮ እጅ ላከበት፤ በደብዳቤውም ላይ፣ ኦርዮን ውጊያው በተፋፋመበት ግንባር መድበው፤ ከዚያም ተወግቶ እንዲሞት ትታችሁት ሽሹ ብሎ ጻፈ።" 2 ሳሙ 11፡14-15

1. 2ኛ ሳሙ 11፡1-27 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-3 ላይ ስናነብ ጊዜው የምን ጊዜ እንደነበረ ነው የምንመለከተው? የእስራኤል ሰራዊትና የዳዊት የጦር አዝማች የሆነው ኢዮአብ የሚገኙት በየት ነበረ?
2. ዳዊት በቁ4 ላይ ስናነብ ዳዊት በሐጥያት እንደወደቀ እንመለከታለን። ከቁ2 ጀምሮ እስከ ቁጥር 5 ባለው ክፍል ውስጥ ዳዊት በሐጥያት ከመውደቁ በፊት ከመጀመሪያው ጀምሮ ያለፈባቸውን ደረጃዎች ቅደም ተከተል ባለው መንገድ ተናገር። ይህ ሰው ሴትየዋ ባለትዳር እንደሆነች ተነግሮታል፣ ባሏ በጦር ሜዳ ላይ እንዳለ ያውቃል፣ አብሯት በመተኛት የማርገዝ ዕድል እንዳለም ሁሉ ያውቃል፤ ታዲያ ለምን ይመስልሃል ይህንን ሁሉ አልፎ ዝሙት ለማድረግ የወሰነው?
3. በቁ6-9 ውስጥ ንጉሥ ዳዊት እውነተኛና ከልብ ያልሆኑ ሲያደር የምንመለከታቸው ንገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። በቁ10-11 ላይ ዳዊት ልክ ለእርሱ ያሰበ በመምሰል "ከመንገድ ገና አሁን መግባትህ አይደለምን? ወደ ቤትህ ያልሄድከው ለምንድነው?" በማለት ለቀረበለት ጥያቄ ኦርዮን የመለሰው መልስ፤ ዳዊት በ2ኛ ሳሙ 7፡1-2 ላይ ከተናገረው አነጋገር ጋራ መመሳሰል የምንመለከትበት በምን መንገድ እንደሆነ ተናገር።
4. ንጉሱ ዳዊት በቁጥር 12 እና 13 ላይ ስናየው አስቀድሞ ባደረገው ሃጥያት ላይ ሲጨምር የምናየው ሌላው ተጨማሪ ሃጥያት ምንድነው? ኦርዮ በቁ11 ላይ ከመስከሩ በፊት ለማድረግ ያልፈለገውና በቁ13 ላይም ደግሞ ከሰከረ በኋላ እንኳን ሊያደርገው እንዳልፈቀደ የምንመለከተው ነገር ምንድነው?
5. በቁ11-13 ላይ ኦርዮ ለእግዚአብሄር ታቦት፣ ለእግዚአብሄር ህዝብና፣ ጌታዬ ለሚለው ለኢዮአብ ያሳየው ጥልቅ ፍቅር በ14-15 ላይ ወርደን ስንመለከት በኦርዮ ሕይወት ላይ ያስከተለው ነገር ምንድነው? የዳዊት የጦር መሪ የሆነው ኢዮአብ ከአለቃው የመጣለትን ትዕዛዝ ተፈጻሚ ሲያደርግ በቁ16-17 ላይ እናያለን፤ ይህ ሰው ሌላ አማራጭ ነበረው ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ። ጠላት ወግቶ እንዲገለው ወንድምህን እንዲጋለጥ ያደረክበት ወይም ደግሞ እንደ ኢዮአብ ሌላው ሊያደርግ ያሰበውን ተፈጻሚ ለማድረግ ለድርጊቱ ተባባሪ የሆንክበት ጊዜ ካለ ከወገኖች ጋራ ተወያዩበት።
6. ቁ18-21 ላይ ስናነብ ዳዊትና የጦር አዛዡ ኢዮአብ፤ የኦርዮን ንጹህ ደም ማፍሰስን አስመልክቶ ሁለቱ ብቻ የሚያውቁት ተጨማሪ ሚስጢር እንደነበራቸው እንረዳለን። ይህ ዳዊትና ኢዮአብ ብቻ የሚያውቁት ሚስጢር ምን ነበረ?
7. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጸሐፊው ንጉሱ ዳዊት ያደረጋቸውን ነገሮች ሁሉ በቅደም ተከተል ከዘረዘረ በኋላ፤ ለምዕራፉ ማጠቃለያ አድርጎ ያሰፈረው ሃሳብ ምን የሚል ነበረ? የዳዊት ህይወት ከእረኝነቱ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በምናውቀው፤ ዳዊት የዚህ ዓይነቱን የድፍረት ሃጥያት ያደረገው በችግሩ ወይስ በሞላለት ሰዓት ላይ ነው? ከዚህ ምን ትምህርት መማር ይቻል ይመስልሃል?
8. ዳዊት በትክክለኛ አዕምሮው ሆኖ ቢያስብ፤ ኦርዮ የዚያን ዓይነት የአገር፣ የህዝብና፣ በተለይም ደግሞ ለእግዚአብሄር ያለውን ፍቅር የሚገልጥ መልስ ሲሰጠው፤ ለሞት ከመዳረግ ይልቅ ማድረግ የነበረበት ነገር ምን ነበረ ብለህ ታምናለህ? ማድረግ ያለብህን ትተህ ማድረግ የማይገባህን እስከታደርግ ድረስ በሐጥያት ታውረህ ታውቃለህ ወይ? ሐጥያት በሰላም ጊዜ እናደርገዋለን ብለን በህልማችን የማናስበውን ነገር ማድረግ እስከንችል ዓይናችንን ሊያሳውር የሚችል ሃይለኛ ጉልበት እንዳለው ልንገነዘብ ያስፈልገናል።

# ጥናት አሥራ ሁለት 2ኛ ሳሙ 12፡1-31

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄርን ቃል ማቃለል ማለት ራሱን እግዚአብሄርን ማቃለል እንደሆነ ነብዩ ለዳዊት እንደነገረው ሁሉ፤ እኛም በህይወታችን የእግዚአብሄርን ቃል በመናቅና በማቃለል እየተመላለስን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከጌታ ጋራ መልካም ግንኙነት እንዳለን መናገር እንደማንችል ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ታዲያ በፊቱ ክፉ ነገር በማድረግ፣ የእግዚአብሄርን ቃል ያቃለልከው ስለምንድነው?...ስለዚህ ሰይፍ ለዘለዓለም ከቤትህ አይርቅም፤ እኔን አቃለኸኛል፤ ሚስት እንድትሆንህም የኬጢያዊውን የኦርዮን ሚስት ወስደሃታልና።" 2ኛ ሳሙ 12፡9-10

1. 2ኛ ሳሙ 12፡1-31 በአንድነት ይነበብ። ምዕራፍ 12 ገና ሲጀምር በቁ1 ላይ "እግዚአብሄር ናታንን ወደ ዳዊት ላከው" ይላል። ይህ ነብይ ወደ ዳዊት መላኩ የእግዚአብሄርን ፍቅር የሚገልጸው በምን መንገድ ነው? ነብዩ ናታን መጥቶ የእግዚአብሄርን መልዕክት ሲነግረውና በእግዚአብሄር ፊት እንደበደለ ሲያስታውቀው፤ በነብዩ በኩል ለመጣለት መልዕክት ምላሽ ለመስጠት ንጉሥ ዳዊት የነበሩት ሁለት አማራጮች ምንና ምን ነበሩ?
2. በቁ1-4 ላይ በምንመለከተው ምሳሌ ውስጥ እግዚአብሄር ዳዊትንና ኦርዮን እንደ ምን አድርጎ ነው እያንዳንዳቸውን ያቀረባቸው? በቁ5-6 ውስጥ በከተማይቱ ይኖሩ ነበረ የተባሉትን የሁለቱን ሰዎች ታሪክ ከናታን ከሰማ በኋላ፤ ዳዊት ስለተሰማው ስሜት ምን ማየት እንችላለን? ይህንን አስከፊ ነገር አደረገ በተባለው ሰው ላይ ዳዊት የፈረደው ፍርድ ምን ነበረ?
3. በቁ7-10 ውስጥ ስናነብ እግዚአብሄር ከዚህ ቀደም ለዳዊት ያደረገለትን ነገሮች በመዘርዘር ሲናገር እንመለከታለን፤ እነዚህ አደርግሁልህ በማለት የሚናገራቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? ቁ9 ላይ ደግሞ እግዚአብሄር ለዳዊት "ኬጢያዊውን ኦርዮን በሰይፍ መታህ...እርሱንም በአሞናውያን ሰይፍ ገደልኸው።" በማለት ይናገራል። ይህንን ሰው ዳዊት በሰይፍ ሲመታ ወይም በሰይፍ ሲገድለው አናይም፤ ታዲያ ለምንድነው ዳዊት ሁኔታውን ለማስተባበል የማይሞክረው?
4. በቁ11 እስከ 14 ላይ ስንመለከት ዳዊት ለፈጸመው ሃጥያት እግዚአብሄር የሚቀጣው ቅጣት ምን እንደሆነ ተዘርዝሯል፤ ዳዊትን የሚጠብቁት ቅጣቶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። በነብዩ በኩል ሃጥያቱ ሲነገረው ዳዊት የወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ ምን ነበረ? ዳዊት ሃጥያቱ ሲነገረው የወሰደውን እርምጃና፤ ከእርሱ በፊት ንጉስ የነበረው ሳዖል በ1ኛ ሳሙ 15፡19-21 ላይ ሃጥያቱ ሲነገረው ያደረገውን በማነጻጸር ተናገር። አንተስ ጥፋትህ ሲነገርህ የመጀመሪያ ምላሽህ ምን ይሆን?
5. ዳዊት ሃጥያቱን በመናዘዙ እግዚአብሄር ሃጥያቱን እንዳስወገደለት ቁ13 ይነግረናል፤ በ1ኛ ሳሙ 15 ውስጥ ሳዖል ሃጥያቱን በሌሎች ላይ በማላከኩ እግዚአብሄር ያስወገደለት ነገር ምን ነበረ? ዳዊት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሰራቸውን ሃጥያቶች የሚገልጽ አንድ ቃል በቁ9፣ ቁ10፣ እና ቁ14 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል፤ ይህ ቃል ምን እንደሆነ ተናገር።
6. በቁ15-23 ላይ ከኦርዮ ሚስት የተወለደው ልጅ ታሞ ለሞት በቀረበበት ሰዓት ዳዊት ሲያደርግ የምንመለከተው ነገር ምንድነው? እግዚአብሄር በቃሉ ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች በጸሎት ወደፊቱ እንድንመጣና እርሱም እንደሚሰማን በማረጋገጥ የተናገረባቸው ብዙ ክፍሎችን መጥቀስ ይቻላል፤ ታዲያ ለምንድነው ዳዊት በዚህ ክፍል ይህንን ያህል ጸሎትና ልመና ሲያደርግ አልሰማ ብሎ ልጁ እንዲሞት የፈቀደው? አንተስ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ምን እንደሆነ እያወቅህ ነገሮች በሌላ አቅጣጫ እንዲሄዱ ትጸልያለህ ወይ?
7. ቁ24-31 ላይ ስናነብ፤ ቤርሳቤህ ለዳዊት የወለደችን ልጅ እግዚአብሄር እንደወደደውና ስሙንም ከሰለሞን ይልቅ ይዲድያ ተብሎ እንዲጠራ እግዚአብሄር በነብዩ በኩል ሲናገር እንመለከታለን፤ እግዚአብሄር ይህንን ልጅ የወደደው ምን ነገር አይቶበት ነው ትላለህ? በቁ27 እና 28 ውስጥ ኢዮአብ ከተማይቱን ይዞ በራሱ ስም እንድትጠራ ከማድረግ ይልቅ በዳዊት ስም እንድትጠራ መልዕክትን መላኩ ምን ያስተምረናል?
8. ቁ9-10 ላይ መለስ ብለን ስንመለከት፤ ዳዊት በቁ9 ላይ የእግዚአብሄርን ቃል እንዳቃለለ፣ በቁ10 ላይ ደግሞ ራሱን እግዚአብሄርን እንዳቃለለ ይነገረዋል። በዚህ ሥፍራ የእግዚአብሄርን ቃል ማቃለል ማለት እንደምን ሆኖ ነው የተነገረው? አንተስ ከእግዚአብሄር ጋራ ጥሩ ግንኙነት እንዳለህ እየተናገርክ፤ ቃሉን ግን ለመታዘዝ እንቢ የምርልበት ጊዜ አለ ወይ? ቃሉን ሳያከብሩ እግዚአብሄርን እወዳለሁ ወይም ከእግዚአብሄር ጋራ ጥሩ ግንኙነት አለኝ ማለት የማይሆን ነገር እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል።

# ጥናት አሥራ ሶስት 2ኛ ሳሙ 13፡1-39

የጥናት ዓላማ፡- ኢዮናዳብ ተንኮለኛ ሰው ሆኖ ሳለ በዳዊት ፊት ቅን በመምሰል የልቡን ሃሳብ ለማስፈጸም እንደሞከረ ሁሉ፤ ዛሬም በዘመናችን ልባቸው በተንኮል የተሞላና የራሳቸውን ፍላጎት ብቻ ለማስፈጸም ማናቸውንም ነገር ከማድረግ የማይመለሱ ሰዎች እንዳሉ ለማሳሰብ።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ኢዮናዳብ ዳዊትን እነሆ የንጉሱ ልጆች መጥተዋል፣ አገልጋይህም እንዳለው ሆኗል አለው።" 2ኛ ሳሙ 13፡35

1. 2ኛ ሳሙ 13፡1-39 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ያሉትን ቁጥሮች ስንመለከት የዳዊት ልጅ አምኖንን ለህመም የዳረገው ነገር ምን ነበረ? አምኖን ይህ እያለፈ ያለበት ሁኔታ ሳይነገረውና እርዳታ ሳይጠየቅ እርዳታን ለመስጠት ራሱን ያቀረበው ሰው ስም ማን ይባላል? ስለዚህ ሰው፤ ማለትም አምኖንን ለመርዳት ስለቀረበው ሰው በቁ3-4 ላይ ከተነገሩት ሃሳቦች ማወቅ የምንችላቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር።
2. በቁ5-7 ላይ በምናነብበት ጊዜ በአምኖን ልብ ውስጥ ለተፈጠረው ሃጥያታዊ ምኞት ጓደኛው ለሆነው ለኢዮናዳብ በነገረው ጊዜ፤ ይህ ሰው መልስ ይሆናል ብሎ የመከረው ምክር ምን ነበረ? ኢዮናዳብ ስለተባለው ሰው ምንም ባናውቅና አንዳችም ባንሰማ፣ ከመከረው ምክር በመነሳት ስለ መንፈሳዊ ህይወቱ ምን መናገር እንችላለን? በአንተስ ህይወት ውስጥ ያሉት አማካሪ ጓደኞችህ ከሃጥያት የሚመልሱህ ናቸው ወይስ ወደ ሃጥያት የሚገፉህ?
3. አምኖንን በቁ7-11 ላይ ስንመለከተው በልቡ የነበረውንና የሚፈልገውን ሃጥያት ለመፈጸም በመጀመሪያ ሲያደርግ የምናየው ነገር ምንድነው? አብዛኛውን ጊዜ ሰው መልካም ነገርን ወይም ደግሞ የጽድቅን ሥራ ሲሰራ ሰዎች መኖራቸውና አለመኖራቸው ብዙም የሚገደው ነገር አይሆንም፤ ታዲያ ለምን ይመስልሃል ይህ ሰው በዚህ ክፍል ውስጥ በአካባቢው ማንም እንዳይገኝና ሰው ሁሉ ከቤቱ እንዲወጣለት የፈለገው?
4. አምኖን በጉልበቱ ተጠቅሞ ሊያደርግ የተነሳውን ድርጊቱን ትዕማር በቁ12-14 ላይ ምን በማለት ነው ስትጠራው የምንመለከተው? ይህንን ሰው ወደ ልቡ ለመመለስ በምታደርገው ሙከራ ትዕማር የጠየቀቻቸው ሶስት ጥያቄዎችን እንመለከታለን፤ እነዚህ ሶስት ጥያቄዎች ምንና ምን የሚሉ ናቸው? ይህች ሴት እነዚህን ጥያቄዎች ከማቅረቧም ባሻገር ለዚህ ሰው የተሻለ መፍትሄ ሊሆን ይችላል ብላ የምትለውንም ሃሳብ አቅርባለታለች፤ ይህ ያቀረበችለት ሃሳብ ምን የሚል ነበረ?
5. በቁ20 ላይ "ያ ወንድምሽ አምኖን ካንቺ ጋር ነበርን?" በማለት አቤሴሎም ትዕማርን መጠየቁ ምን የሚጠቁመን ነበር ይኖራል ብለህ ታስባለህ? በዚሁ ቁጥር ላይ ስንመለከት አቤሴሎም ለእህቱ ለትዕማር የሆነውን ሁኔታ በልቧ እንዳታኖረውና በአምኖን ላይ ቂም እንዳትይዝበት ሲመክራት እናነባለን፤ ቁ22ትን ግን ስንመለከት አቤሴሎም ራሱ ለአምኖን በልቡ ውስጥ የጥላቻ አመለካከት እንደነበረው እናያለን። አምኖን ለእህቱ ያንን ዓይነት ምክር ሲመክር፤ በሌላ በኩል ምን ማለቱ ነበረ?
6. ሰዎች ምንጊዜም ግብዣን ሲያደርጉ ከቤተሰቦቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ወይም ከጎረቤቶቻቸው ጋራ የደስታ ጊዜ ለማሳለፍ እንደሆነ እናውቃለን። በ23-29 ያሉትን ቁጥሮች ስናነብ አቤሴሎም ቤተሰቦቹን ለግብዣ ሲጠራ እንመለከታለን፤ ይህን ግብዣ ልዩ ያደርገዋል ብለህ የምታምነው ነገር ካለ ተናገር። በትክክለኛው ቦታና ለመልካም ነገር ስንጠቀምበት ለሌሎች በረከት ሊሆን የሚችለውን ነገር አቤሴሎም በቁ28 ላይ ለከፋት መሳሪያ አድርጎ ሲጠቀምበት የምታየው ነገር ምንድነው?
7. አስቀድሞ ለንጉሥ ዳዊት የደረሰው ዜና ምን የሚል ነበረ? ዘግይቶ የመጣውን ማለትም የሞቱት የዳዊት ልጆች ሁሉ ሳይሆኑ አንዱ ልጁ አምኖን ብቻ እንደሆነ የሚያስታውቀውን ዜና ያመጣው ሰው ማን ይባላል? ይህ ሰው የአምኖን የቅርብ ወዳጅ እንደነበረና ተንኮለኛም ሰው እንደነበረ ከቁ3 መረዳት የምንችል ሲሆን፣ ኢዮናዳብ በዚህ በተፈጠረው ሁኔታ ሁሉ ውስጥ ስንመለከተው ተንኮለኛነቱ ጉልህ ሆኖ የሚታየው እንዴት ነው?
8. ኢዮናዳብን በቁ3 ላይ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ተመልክተናል፤ ታዲያ በቁ35 ላይ ይህ ሰው በንጉሥ ፊት ምን ዓይነት ሰው መስሎ ለመታየት ነው የሞከረው? ከሌሎች ጋራ ሌላ ነገር እያደረጉ በአንተ ዘንድ ግን ራሳቸውን ቀይረው ሌላ የሚናገሩ ሰዎች ገጥመውህ ያውቃሉ ወይ? በዘመናችንም ሁለት አይነት የተለያየ ህይወትና ፊት የሚያሳዩ ብዙ ሰዎች ስላሉ በጥንቃቄ መመላለስ ያስፈልገናል።

# ጥናት አሥራ አራት 2ኛ ሳሙ 14፡1-33

የጥናት ዓላማ፡- ምንም እንኳን በዳዊት ቤተሰብ መሃል የተከሰተው ሁኔታ ኢዮአብን ባይመለከተውም፤ ሁኔታውን ለመቀየር የሚቻለውን እንዳደረገ ሁሉ፤ አንዳንድ ጊዜ በቅዱሳን መሃል የሚፈጠረው አለመግባባት እኛን የሚመለከተን ነገር ሆኖ ባናየውም እንኳን፤ ሁኔታውን ለማርገብና እርቅን ለመፍጠር የሚቻለንን ሁሉ ማድረግ እንደሚኖርብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "አዎን ይህንን እንዳደርግ ያዘዘኝና ይህም ሁሉ ቃል በእኔ በአገልጋይህ አንደበት እንዲነገር የላከኝ ኢዮአብ ነው። አገልጋይህ ኢዮአብ ይህን ያደረገውም ያለውን ሁኔታ ለመለወጥ ሲል ነው።" 2ኛ ሳሙ 14፡19-20

1. 2ኛ ሳሙ 14፡1-33 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-3 ላይ ስንመለከት ኢዮአብ ወደ ዳዊት መልዕክተኛ መላክ የወሰነው መቼ ነበረ? ይህ ዛሬ ኢዮአብ የወሰደው እርምጃ ቀደም ብሎ ገና ሁኔታው እንደተፈጸመ አካባቢ ቢያደርገው ኖሮ አሁን ከተገኘው ውጤት የተለየ ሊሆን ይችል የነበረበትን ሁኔታ አስረዳ። ከዚህ ሁኔታ ለራሳችን ልንማረው የምንችለው ምን እውነት ይታይሃል?
2. ንጉሡ ዳዊት በቁ4-7 ላይ ከዚህ ቀደም መልዕክት መጥቶለት በሚያውቀው መንገድ ከአገር ስለተሰደደው በልጁ ነገር ላይ ውሳኔ እንዲያደርግ ሲገደድ ነው የምንመለከተው፤ ከዚህ ቀደም በዳዊት ህይወት ውስጥ በዚህ ዓይነት መንገድ መልዕክት የመጣለትን ጊዜ ሁኔታው ምን ይመስል እንደነበረ አስረዳ። ይህች ሴት ራሷን ያቀረበችው እንደ መበለት ወይም ባል እንደሌላት ሆና ነው፤ ታዲያ ሴቲቱ ራሷን በዚህ ዓይነት ማቅረቧ በንጉሥ ፊት ይዛ ለመጣችው ነገር እንዴት ሊጠቅማት ይችላል ብለህ ታምናለህ?
3. በቁ8-12 ላይ ሴቲቱና ንጉሥ ዳዊት ሃሳብ ሲለዋወጡ እንመለከታለን። ሴቲቱ በኢዮአብ እንደተመከረችው ዳዊትን ወደ ፈለገችበት ቦታ እንዳደረሰችው የተረዳችው የትኛውን ንግግር በተናገረ ጊዜ ይመስልሃል?
4. በቁ14 ላይ ሴቲቱ በፍጥነት እርቅ የማድረግን አስፈላጊነትና እርቅን ለማድረግ ደግሞ ጊዜን ማራዘም መልካም ነገር እንዳልሆነ ለንጉሱ ለማስገንዘብ የተጠቀመችበት ምሳሌ ምን የሚል ነበረ? ዳዊት ከሞተ እርቅ የሚለው ነገር ሊኖር እንደማይችልና በፍጥነት መደረግ ያለበት ነገር እንደሆነ ለማስገንዘብ ለዳዊት ያስተላለፈችው ጥበብ የተሞላ ምክር በእኛ ህይወትስ በምን መንገድ ልንጠቀምበት እንችላለን ትላለህ?
5. በቁ19-27 ላይ ስንመለከት ኢዮአብና የቴቁሔዊቱ ሴት ያሰቡት ነገር እንደተሳካላቸውና ንጉሱ ልጁን አቤሴሎምን ከስደት ለማስመጣት ፈቃደኛነቱን አስታውቋል። በዚህ ክፍል ውስጥ ንጉሥ ዳዊት ከአቤሴሎም መምጣት ጋራ አያይዞ ለሚያመጡት ሰዎች የሰጠው አንድ መመሪያ ምን ነበረ? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለ አቤሴሎምና ስለ ቤተሰቡ የተነገሩትን ነገሮች አጠር ባለ መንገድ ለመናገር ሞክር።
6. በቁ28-33 ላይ በሚገኘው ክፍል ውስጥ ስንመለከት በተለይም ቁ32 ላይ አቤሴሎም እያወዳደረ ሲናገር የምናያቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እግዚአብሄር አምላክ እኛን ይቅር ማለቱን ይቅር ብያችኋለሁ፤ መታረቁንም ታርቀናል፣ ነገር ግን ወደ እኔ መቅረብ አትችሉም፤ እዚያው በሩቁ ባላችሁበት እንጂ ፊቴን አታዩም ቢለን አሁን ካለን ዕድል ጋራ ሲነጻጸር እንዴት ታየዋለህ?
7. በቁ20 ላይ መለስ ብለን ስንመለከት የንጉሱ የጦር መሪ የነበረው ኢዮአብ እኔን አይመለከተኝም ማለት በሚችለው ነገር ውስጥ ገብቶ ይህንን ሁሉ ነገር ለማድረግ የወሰነው ለምን ነበረ? አንተስ በእግዚአብሄር ቤተሰቦች መሃል የማያስፈልግ ክፍተት እንደተፈጠረ ስታውቅ ሁኔታውን ለመቀየር ጥረት ታደርጋለህ ወይስ አያገባኝም በማለት ጥግህን ይዘህ ትኖራለህ? በቅዱሳን መሃል የሚፈጠረው ማናቸውም ዓይነት መገፋፋትና የልብ መራራቅ ሁላችንንም የሚመለከት ስለሆነ የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል።

# ጥናት አሥራ አምስት 2ኛ ሳሙ 15፡1-37

የጥናት ዓላማ፡- አባቱ ለእግዚአብሄር ያለውን ልብ የተረዳው አቤሴሎም፤ የእግዚአብሄርን ስም ለተንኮሉ ማስፈጸሚያ መሳሪያ አድርጎ እንደተጠቀመ ሁሉ፤ ዛሬም በቤተክርስትያን የራሳቸውን የልብ ፍላጎት ለማሳካት የእግዚአብሄርን ስምና ለስላሳ መንፈሳዊ ቋንቋን ሽፋን በማድረግ ቅዱሳንን የሚያታልሉ ደፋሮች እንደማይጠፉ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እኔ አገልጋይህ በሶርያ ምድር በጌሹር ሳለሁ፤ እግዚአብሄር ወደ ኢየሩሳሌም የመለሰኝ እንደሆነ በኬብሮን ለእግዚአብሄር እሰግዳለሁ ብዬ ተስያለሁ።" 2ኛ ሳሙ 15፡8

1. 2ኛ ሳሙ 15:1-37 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ውስጥ አቤሴሎም ከአባቱ ከዳዊት ጋራ ከታረቀና ፊቱን ማየት ከተፈቀደለት በኋላ ማድረግ የጀመረውን ነገር እንመለከታለን። ይህ ሰው በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስናየው ማድረግ የጀመራቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። አቤሴሎም በልቡ የነበረውና ለሰዎቹ ያልተገለጠው ፍላጎቱ ምን ነበረ?
2. አቤሴሎም የልቡን ፈቃድ ከግብ ለማድረስ ከላይ ካነበብናቸው ሃሳቦች ሌላ ያደርግ የነበረው ነገር እንደነበረ ቁ5-9ን ስናነብ እናገኛለን። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የልቡን ሃሳብ ለማስፈጸም ሌላ ይጠቀምበት የነበረው ስጋዊ ዘዴ ወይም ጥበብ ምን ታያለህ? አቤሴሎም በአባቱ ላይ የሸረበውን ተንኮል በተግባር ለመፈጸም ወደ ኬብሮን ለመሄድ ከንጉሱ ፈቃድ እንዲሰጠው ያቀረበው ምክንያት ምን የሚል ነበረ? ያቀረበው ምክንያት ለማመን የሚያስቸግርና እውነተኛነቱ የሚያጠራጥረው ለምንድነው?
3. ቁ10-12 ላይ ስናነብ በዚህን ወቅት ከአቤሴሎም ጋራ በሴራው ተሳታፊ የነበሩ ሰዎች እነማን ነበሩ? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በሰዎች አመለካከት አቤሴሎም ብዙ ብልጠት ወይም ጥበብ የተሞላባቸው የሚመስሉ ድርጊቶችን ሲያደርግ እናያለን፤ የዚህን ሰው ድርጊት በያዕ 3፡14-17 በሰፈረው ሃሳብ ስትመዝነው፤ የአቤሴሎምን ድርጊቶች በየትኛው ጎራ ውስጥ መመደብ አለብን ትላለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ።
4. ቁ13-18ትን በተለይም ደግሞ ቁ16 ላይ ስናነብ "ቤተ መንግሥቱን እንዲጠብቁ አሥር ቁባቶች አስቀረ" የሚል ነገር እናነባለን። ኢየሩሳሌምን ለመጠበቅ እውነት ዳዊት በትክክለኛ አዕምሮ አስቦ አሥር ቁባቶች መጠበቅ ይችላሉ ብሎ አምኖበት ይመስልሃል፤ ወይስ ከበስተኋላው ሌላ ነገር አለ ብለህ ታምናለህ? አስረዳ
5. በቁ19-21 ላይ ስናነብ፤ ዳዊት ጌታዊውን ኢታይን ባነጋገረበት ወቅት ተመልሶ ከአቤሴሎም ጋራ እንዲኖር ሲነግረው፤ አቤሴሎምን እንደምን አድርጎ ነው ያቀረበለት? በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ስትመለከት፤ ይህ የጌት ሰው የሆነው ኢታይ ለዳዊት መልስ ሲሰጥ አቤሴሎምን አስመልክቶ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ዳዊት የተናገረውን የተቃወመው በምን መንገድ ነው? ቁ21ድን በምታነበበት ጊዜ የኢታይን አነጋገር የሚመስል የምታስታውሰው ምን ታሪክ እንዳለ ተናገር።
6. ቁ25-26 ላይ እስራኤላውያን አብዛኛውን ጊዜ በጦርነት ድል ለማግኘት ሲፈልጉ የቃል ኪዳኑን ታቦት ሲያስመጡ እንጂ ታቦቱን መልሰው ሲሰዱ አናይም፤ በዚህ ክፍል ግን ዳዊት ታቦቱን መልሰው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲወስዱ ሲያዝ እናያለን። ከዚህ አድራጎቱ ስለ ዳዊት የምንማረው አንድ ትልቅ ነገር ምንድነው? አንተስ እምነትህ በእግዚአብሄር በራሱ ላይ ነው ወይስ በጸሎት፣ በቃሉና በመሳሰሉት ወደ እርሱ እንድንቀርብባቸው በተሰጡን ነገሮች ነው?
7. በቁ31 ላይ ከአቤሴሎም ጋራ ካሴሩት መሃል ቀድሞ የእርሱ አማካሪ የነበረው አኪጦፌል እንደነበረ ሲነገረው ዳዊት ቶሎ ብሎ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ?
8. ቁ7-8ትን መለስ ብለን ስንመለከት፤ አቤሴሎም አባቱ የእግዚአብሄር ፍርሃት በልቡ የሞላበት ሰው መሆኑን ስላወቀ፤ ለተንኮሉ ማስፈጸሚያ እንዲሆን በሁለቱ ቁጥሮች ውስጥ ብቻ የእግዚአብሄርን ስም ስንት ጊዜ ሲጠቀም ታያለህ? አንተስ በህይወትህ የእግዚአብሄርን ቅዱስ ስም የልብህን መሻት ለማስፈጸም መሳሪያ አድርገህ የመጠቀም ልምድ አለህ ወይ? በተለይም እንደ ንጉስ ዳዊት የእግዚአብሄር ፍርሃት እንዳለባችሁ ሲረዱ፤ በእግዚአብሄር ሥም የተለያየ ተንኮል ማድረግ የማይከብዳቸው ሰዎች ስላሉ እንጠንቀቅ።

# ጥናት አሥራ ስድስት 2ኛ ሳሙ 16፡1-23

የጥናት ዓላማ፡- ሲባ የተባለው ሰው፤ እንደ አባትና ልጅ በፍቅር የኖሩትን ዳዊትንና ሜምፊቦስቴን በውሸት መለያየት እንደሞከረ ሁሉ፤ ዛሬም የራሳቸውን መሻት ለማስፈጸም፤ በወንድማማች መሃል ጠብን የሚዘሩ፣ አንድነትንና ፍቅርን ለማደፍረስም ወደኋላ የማይሉ ብዙዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ፤ ቸኩሎ እርምጃ ከመውሰድ መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እርሱም እንዲህ አለው፡- ጌታዬ ንጉስ ሆይ፤ እኔ አገልጋይህ ሽባ በመሆኔ፤ ከንጉሥ ጋር መሄድ እንድችል አህያዬ ይጫንልኝና ልቀመጥበት ብዬ ነበር፤ ይሁን እንጂ አገልጋዬ ሲባ አታለለኝ።" 2ኛ ሳሙ 19፡26

1. 2ኛ ሳሙ 16፡1-23 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ሲባ የተባለው የሜምፊቦስቴ አገልጋይ ንጉሥ ዳዊትን ለመቀበል ይዞ የቀረበው ነገር ምን ነበረ? አስቀድሞ የነበረህን የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት በመጠቀም፤ ሜምፊቦስቴ የተባለው ሰው ማን እንደሆነና ከዳዊት ጋራ ያለውን ግንኙነት ተናገር። ሲባ ለንጉሱ እጅ መንሻ ይዞ በመጣው ነገርና ስለ ጌታው ስለ ሜምፊቦስቴ ተጠይቆ በሰጠው መልስ ምክንያት ያተረፈው ምን ነገር ታያለህ?
2. ሳሚ የተባለው ሰው በቁ5-8 ላይ ስንመለከተው ንጉሥ ዳዊትን በመኳንንቱና በመሳፍንቱ ሁሉ ፊት ይራገም እንደነበረ እናነባለን። ማናችንም የዚህን ሰው የልብ ሃሳብ ማወቅ ባንችልም እንኳን፤ ሳሚ ዳዊትን ለመርገም ያነሳሳው ነገር ምን ሊሆን ይችላል ብለህ ታምናለህ? ሳሚ በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ስለ ዳዊት ማንነትና፣ ዳዊት አደረገ ብሎ ስላመነባቸው ነገሮች የሚናገራቸውን ጥቂቶቹን በመዘርዘር ተናገር።
3. በቁ7-8 ላይ ተራጋሚው ሳሚ በንጉሥ ዳዊት ላይ ካዥጎደጎዳቸው የእርግማን ዓይነቶች መሃል፤ በአንተ አመለካከት የትኞቹ እርግማኖች እውነትነት ሊኖራቸው ይችላል ብለህ ታምናለህ? ከእርግማኖቹ መሃልስ በእርግጠኛነት፤ ይህ ዳዊትን ሊመለከት አይችልም ብለህ የምትላቸው እርግማኖች ካሉ ተናገር። ሳሚ ዳዊትን በመኳንንቱ ሁሉ ፊት እንዳዋረደው፤ አንተስ በዝምድና፣ በአገር ልጅነት፣ በዘር፣ ወይም በመሳሰለ ምክንያት በመነሳት የእግዚአብሄርን ሰዎች ለማቃለል ምን ልብህ ይደፍራል?
4. ቁ9 እና ቁ10 ላይ ንጉሥ ዳዊትን የተራገመው ሳሚ ሊወሰድበት ስለሚገባው እርምጃ፤ በጽሩያ ልጅ በአቢሳ እና በዳዊት መሃል የምንመለከተው የአመለካከት ልዩነት ምን እንደሆነ አስረዳ። በቁ11-12 መሰረት፤ የሳሚ እርግማን ለዳዊት አስገራሚ እንዳልሆነና እርግማኑን ያመጣው ሰው ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ እንዳይወሰድበት አቢሳንም ሆነ መኳንንቱን ለመከላከል ለማሳመን የተጠቀመበት ሃሳብ ምን ነበረ?
5. በ15-19 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት ከልቡ ይመንበትም አይመንበት፤ ኩሲ ለዳዊት ከነበረው ወዳጅነት አንጻር ምን ማድረግ እንደነበረበት ነው በጥያቄ መልክ የሚያቀርብለት? ይህ ዓይነቱ አመለካከት በምን መንገድ ነው በምሳሌ 17፡17 ላይ ከተነገረው "ወዳጅ ምን ጊዜም ወዳጅ ነው" ከሚለው ሃሳብ ጋራ እንዴት ሊሄድ እንደሚችል አስረዳ። አንተስ ጓደኝነትህን በዚህ የእግዚአብሄር ቃል አንጻር ስትመዝነው እንዴት ታገኘዋለህ?
6. ቁ20-23ትም ስናነብ ዳዊት በእግዚአብሄር ላይ ሐጥያትን በማድረጉ ምክንያት በነብዩ በናታን አማካኝነት የተነገረው ትንቢት እየተፈጸመ እንደሆነ የሚያሳየን የትኛው ሁኔታ ነው? በ2ኛ ሳሙ 15፡31 ዳዊት የአኪጦፌል ከአቤሴሎም ጋራ መሰለፍ እንዳሳሰበውና ወደ እግዚአብሄር ለመጸለይ እንደተገደደ እናያለን፤ እነዚህን ቁጥሮች ስናነብ ዳዊት አኪጦፌልን ለመፍራት ጥሩ ምክንያት እንደነበረው የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው?
7. በቁ3 ላይ ስንመለከት ዳዊት ሲባን ሜምፊቦስቴ ለምን ከዳዊት ጋራ እንዳልመጣ ሲጠይቀው የመለሰውን መልስና፤ በ2ኛ ሳሙ 19፡26 ላይ ሲባ ራሱ ለምን ከዳዊት ጋራ እንዳልተሰደደ የተናገረውን ስናነብ ሲባ ስለተባለው ሰው ባህርይ ምን መማር እንችላለን? በሌላው ሰው ላይ በመዋሸት ለመከበርና ለማደግ የሚንጠላጠል ሰው ገጥሞህ ያውቃል ወይ? በምሳ 6፡16-19 እንደምናነበው፤ በወንድማማች መሃል ጠብን መጫር እግዚአብሄር የሚጸየፈው ነገር መሆኑን ልናስታውስ ይገባና።

<u>ጥናት አሥራ ሰባት 2ኛ ሳሙ 17፡1-29</u>

የጥናት ዓላማ፡- አኪጦፌል በአዕምሮው እውቀት የላቀ ሆኖ የእግዚአብሄርን ሃሳብ ግን እንደሳተ ሁሉ፤ ሰው በአስተሳሰቡ እና በእውቀቱ ከሌሎች ሁሉ የተሻለ መሆኑ የእግዚአብሄርን ሃሳብና ፈቃድ የመረዳት ችሎታ አለው ማለት ላይሆን እንደሚችል እንማራለን።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "አኪጦፌል አቤሴሎምን እንዲህ አለው፤ አሥራ ሁለት ሺህ ሰው መርጬ በዛሬይቱ ሌሊት አባትህን አሳድደዋለሁ፤ በደከመውና አቅም ባነሰው ጊዜም አደጋ እጥልበታለሁ።" 2ኛ ሳሙ 17፡1

1. 2ኛ ሳሙ 17፡1-29 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ላይ አኪጦፌል ለአቤሴሎም የመከረውን ምክር ስንመለከት፤ በአኪጦፌል አመለካከት ዳዊት በዚህን ሰዓት የሚገኘው በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? የአኪጦፌልን አነጋገር በነዚሁ ቁጥሮች ላይ ስናይ፤ አቤሴሎም ዳዊትን ተከትለው ከሄደው ህዝብ መካከል ምን ያህል ሰዎችን ለመጨረስ እንደፈለገ ነው የሚነግረን? እንደገና እነዚህኑ ቁጥሮች በመመልከት፤ አኪጦፌል የነደፈው የጦር ስልት ምን ያህል ተቀባይነት እንደ ነበረው ነው የምናየው?
2. በምሳ 11፡14 ዓይን ስንመዝነው አቤሴሎም በቁ5-6 ላይ የወሰደውን እርምጃ እንዴት ትመለከተዋለህ? አቤሴሎም በዚህን ጊዜ ከአኪጦፌል በተጨማሪ ኩሲን ምክር እንዲሰጠው የፈለገበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል? ቁ7-10ን ስታነብ አርካዊው ኩሲ በአቤሴሎም ፊት ተጠርቶ ምን ማድረግ እንደሚገባው ሃሳብ በተጠየቀበት ወቅት፤ በተለይም ስለዳዊት ማንነትና የዳዊትንም አስተሳሰብ ጨምሮ የሰነዘራቸው ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር።
3. በቁ11-14 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ በማንበብ እግዚአብሄር አምላክ ጸሎትን የሚሰማና የሚመልስ መሆኑን የሚጠቁምህ የትኛው ሃሳብ ነው? ንጉሥ ዳዊት በሃዘን፣ በድካምና እንዲሁም ልቡ በተሰበረበት በዚህ ወቅት ላይ እግዚአብሄር እንዳልተወውና በእርሱ ወገን ተሰልፎ ሥራውን እየሰራለት እንደሆነ የምናየው እንዴት ነው? አንተስ ልብህ ተስፋ በቆረጠበትና እግዚአብሄር የረሳህ በሚመስልህ ወቅት እንኳን ከበስተኋላ ሆኖ ሥራህን እንደሚሰራ ምን ያህል ትገነዘባለህ?
4. ቁ15-19 ላይ የምንመለከታቸው ሰዎች እየኖሩ ያሉት በአቤሴሎም መንግሥት ውስጥ ሆኖ እያለ፤ ራሳቸውን ያስገዙትና እንደ ንጉሳቸው አድርገው የሚናገሩት ግን ማንን ነው? እኛም ብንሆን ምንም እንኳን ኑሯችን በዚህች ዓለም ውስጥ ቢሆንና ሊያስተዳድረን የሚፈልግ የዚህ ዓለም ገዢ ቢኖር እንኳን፤ እኛ ግን ንጉሳችን አድርገን የተቀበልነው ዛሬ ከእኛ ጋራ እንዳለ የማናየውና ነገ ግን ተመልሶ የሚመጣው ንጉሳችን እንደሆነ እውቅና እንሰጠዋለን።
5. በቁ18-20 ላይ ከምናነበው ታሪክ ጋራ የሚመሳሰል ሌላ የምታስታውሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚገኝ ታሪክ ካለ ተናገር። አኪማአስና ዮናታን ሁለቱም የእግዚአብሄር ካህናት እንደሆኑ ይታወቃል፤ በዚህ ቦታ ላይ እነዚህ ሁለት ሰዎች እያደረጉ ያሉት ነገር ምን ያህል ከክህነት ሥራቸው ጋራ ይሄዳል ብለህ ታምናለህ?
6. ቁ17-22 ትን ስንመለከት፤ ከዳዊትና ከእርሱ ጋራ ለነበሩት ሰዎች ህይወት መትረፍ ምክንያት ሆነዋል የምትላቸውን ሰዎች በሙሉ በመዘርዘር ተናገር።
7. ቁ23 ላይ ስለ አኪጦፌል ከምናነበው ሃሳብ በመነሳት፤ በሰዎች ሁሉ ዘንድ ከፍ ከፍ ማለቱና ስለእርሱ ብዙ መነገሩ በዚህ ሰው ላይ ምን ዓይነት ውጤት አስከትሏል ትላለህ? ዳዊት የቀድሞውን የንግሥና ቦታ እንዳጣ በተመለከቱ ጊዜ በጊዜው ከፍ ከፍ ወዳለው ወደ አቤሴሎች እንደተጠጉ ተመልክተናል፤ በቁ27-29 ላይ የምናያቸውን ሰዎች ልዩ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድነው ትላለህ?
8. ወደ ቁ1 መለስ ብለን ስንመለከት፤ አኪጦፌል እግዚአብሄር በቀባው በዳዊት ላይ ተነስቶ ሊገድለው ከአቢሴሎም ጋራ ሲማከር ይታያል። አኪጦፌል በምክሩ በአቤሴሎምም ሆነ በዳዊት ዘንድ የተደነቀ ሆኖ ሳለ፤ እግዚአብሄር ከመረጠው ከዳዊት ጋራ መቆም ሲገባው ከአመጸኛው ከአቤሴሎም ጋራ መቆሙ ምን ያስተምረናል? በምድራዊ ነገር ባላቸው ቦታ በማየት፤ በእግዚአብሄር ቤት ላይ መሪዎች ሆነው የተሾሙ ሰዎች ገጥመውህ ያውቃሉ ወይ? ምድራዊ ችሎታን ለእግዚአብሄር አገልግሎት ማዋል ቢቻልም እንኳን፤ ምድራዊ እውቀት አለን ማለት ግን መንፈሳዊን ነገር መረዳት እንችላለን ማለት እንዳልሆነ ልንገነዘብ ያስፈልገናል።

# ጥናት አሥራ ስምንት 2ኛ ሳሙ 18፡1-33

የጥናት ዓላማ፡- በዳዊት ፊት አኪማአስ መልካም ጥሩ መንፈሳዊ አመለካከት ያለው ሰው ሆኖ ፍሬ ነገር እንዳላገኘበት ሁሉ፤ በቤተ ክርስትያን ውስጥም መልካምና መንፈሳዊያን ሆነው የተሰጣቸውን ሃላፊነት ለመወጣት ጥረት የማያደርጉ ሰዎችም የመሪዎቻቸውን ልብ የማያሳርፉ እንደሆኑ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ንጉሡም ብላቴናው አቤሴሎም ደህና ነውን? ሲል ጠየቀ፤ አኪማአስም ኢዮአብ የንጉሡን አገልጋይና እኔን ባሪያህን ሲልክ ሲል ትልቅ ሁካታ አይቻለሁ፤ ምን እንደሆነ ግን አላውቅም ብሎ መለሰ፤ ንጉሡም እልፍ በልና ቁም አለው።" 2ኛ ሳሙ 18፡29-30

1. 2ኛ ሳሙ 18፡1-33 በአንድነት ይነበብ። ምዕራፍ 18፡1-3 ያለውን ስናነብ፤ ዳዊት የማልቀስ፣ የሸሽትና፣ ለራሱ የማዘኑ ጊዜ አብቅቶ ለጦርነት የመዘጋጀት ጊዜ እንደሆነ መወሰኑን የምናየው እንዴት ነው? ሕዝቡ ዳዊት ከእነርሱ ጋራ ወደ ጦር ሜዳ እንዲሄድ ፈቃደኞች አልነበሩም፤ ለምን ነበረ ህዝቡ ዳዊት ከእነርሱ ጋራ ወደ ጦርነቱ እንዲሄድ ያልፈለጉት?
2. ከአቤሴሎም በመሸሽ ላይ የነበረው ዳዊት ሰራዊቱን ማደራጀት በጀመረበት ወቅት በሰራዊቱ ላይ በዋነኛነት የሾማቸው ሶስት ሰዎች ማን ማን በመባል ይጠራሉ? ዳዊት በቁ4-5 ላይ ስለ ልጁ ስለ አቤሴሎም ለሰራዊቱ የሰጠውን ትዕዛዝና፤ በ2ኛ ሳሙ 17፡1-4 ደግሞ አባቱን ዳዊትን አስመልክቶ የአቤሴሎም መሻት ምን እንደሆነ በአኪጦፌል አንደበት የተነገረውን ቃላት ስናነጻጽር ምን ልዩነት ታያለህ?
3. ከቁ6-8 ያለውን ስንመለከት በወንድማማች መሃል በተካሄደው ጦርነት በተለያየ መንገድ የሞተው ሰው ቁጥር ቢያንስ ምን ያህል ነበረ ትላለህ? ወንድም ወንድሙን እንዲገድልና የዚህን ያህል ሰው ህይወት እንዲጠፋ ሕዝቡን ለዚህ ጦርነት የዳረገውና ለጠፋው ህይወት ሁሉ ተጠያቂው ማን ነው ብለህ ታምናለህ? የልባችንን መሻት ለማስፈጸም ስንል በወንድማማች መሃል ፀብን ከመዝራት እግዚአብሄር አምላክ ይጠብቀን።
4. ቁ9-13 ላይ አቤሴሎምን ስለመግደል አስመልክቶ በጦር መሪው በኢዮአብና ስሙ ባልተጠቀሰ በአንድ ሰው መሃል የተደረገውን ውይይት እናነባለን፤ ሰውየው አቤሴሎምን ገድሎት ቢሆን ኖሮ ኢዮአብ ምን ያደርግለት እንደነበረ ነው የሚናገረው? ይህ ስሙ ያልተጠቀሰ ሰው ምንም ያህል ቢከፍለው ያንን አይነት ድርጊት እንደማይፈጽም የሰጠው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን የሚሉ ነበሩ?
5. በ2ኛ ሳሙ 24፡3 ላይ ኢዮአብ ሲመክር ያልተሰማበትን፤ እዚህ ሥፍራ በቁ12-18 ላይ ደግሞ ኢዮአብ የገባውን ቃል እንዲጠብቅ ሲመከር ለመስማት እንቢ ያለበትን ሁኔታ እናነባለን። በኢዮአብ ላይ የምናያቸው እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ስለሰው ልጅ ባህርይ ምን ሊጠቁመን ይችላል? ቁ19 እና 20ን ስናነብ ኢዮአብ ዛሬ ለዳዊት የምሥራች ቀን አይደለም በማለት አኪማአስን እንዳይሮጥ የከለከለበት ምን የሚያውቀው ምክንያት ነበረው?
6. ቁ21-23 ላይ በምናያቸው ሁለት ሰዎች መሃል የምታያቸውን ልዩነቶች በመዘርዘር ተናገር። በቁ22 ላይ ከኢዮአብ አነጋገር እንደምንረዳው፤ አኪማአስ ይህንን ዜና ለዳዊት ሮጦ በመንገሩ ከዳዊት የሚጠብቀው ምን ነገር እንዳለ ነው የሚጠቁመን? ቁ23 ላይ አኪማአስ ኢትዮጵያዊውን በአቋራጭ ሮጦ እንደቀደመው፤ ቦታቸው ሳይሆን በአነጋገርና በአፋቸው ፈጣኖች ስለሆኑ ብቻ በአቋራጭ በሌላው በተሰጠው ነገር ላይ እጃቸውን ማስገባት የሚወዱ ሰዎች ገጥመውህ ያውቃሉ ወይ?
7. ቁ24-27 ላይ ስንመለከት ንጉሱ ዳዊት በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ሆኖ የጦር ሜዳ ዜና ለመስማት በሚጠብቅበት ወቅት፤ መልካም ዜና ይመጣል ብሎ በልቡ ያመነባቸውን ሁለት ዓይነት መንገዶች ክፍሉ ያሳየናል፤ እነዚህ ሁለቱ መንገዶች ምንና ምንድናቸው?
8. ቁ28-30 ላይ አኪማአስ በጦርነቱ ለተገኘው ድልና መሳካት ክብሩን ሲሰጥ የምናየው ለማን ነው? ይህ ሰው መልካም መንፈሳዊ አመለካከት እንዳለው ቢታይም ቢሆንም የተላከበትን ተልዕኮ ግን ተወጥቷል ብለህ ታምናለህ ወይ? መልካም መንፈሳዊ ህይወትን እየኖረ፤ ነገር ግን ከቤተ ክርስትያን የተቀበለውን አደራና ሃላፊነት በሚገባ ለመወጣት ጥረት ለማድረግ የማይሞክር አማኝ የመሪዎችን ልብ አያሳርፍም።

# <u>ጥናት አሥራ ዘጠኝ 2ኛ ሳሙ 19፡1-43</u>

የጥናት ዓላማ፦ አንዳንድ ጊዜ እንደ ኢዮአብ ለመዋጥ የሚያስቸግረንን እውነት ለመናገር የማይፈሩ ወንድሞች ከጎናችን በመኖራቸው እግዚአብሄር ልናመሰግን እንጂ እንደተቀናቃኝ በመቁጠር ከአካባቢያችን ለማስወገድ መሞከር ሞኝነት እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፦ "…ዛሬ አቤሴሎም በህይወት ኖሮ እኛ ሁላችን አልቀን ቢሆን ደስ እንደሚልህ በዛሬው እለት ለማየት በቅቻለሁ። በል አሁን ተነስተህ ውጣና ሰዎችህን አበረታታ፤ ባትወጣ ግን በዚህች ሌሊት አንድም ሰው አብሮህ እንደማይሆን በእግዚአብሄር እምላለሁ።" 2ኛ ሳሙ 19፡6-7

1. 2ኛ ሳሙ 19፡1-43 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ላይ ስንመለከት ከዳዊት ጋራ የነበረው ሰራዊት የሚገኘው በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነበረ? ኢዮአብና የጦር ሰራዊቱ ከአቤሴሎም ሰራዊት ጋራ ያካሄዱትን ጦርነት በድል በማገባደዳቸው ወደ ከተማቸው ሲመለሱ የጠበቁት ነገር ምን ይመስልሃል?
2. ኢዮአብ በቁ6 ላይ "የሚጠሉህን ትወዳለህ፤ የሚወዱህን ትጠላለህ" በማለት ስለ ንጉሥ ዳዊት የተናገረው አነጋገር በአንተ አመለካከት እውነትነት አለው ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ። በቁ5-8 መሰረት ዳዊት ንጉስ ሆኖ ሳለ የኢዮአብን ምክር በመስማት ስለ ልጁ ማልቀሱን ትቶ ህዝቡን ለማበረታት መውጣቱ ስለዳዊት ማንነት ምን የሚነግረን ነገር ታያለህ? አንተስ ከአንተ የበታች የሆኑ ሰዎች የሚመክሩህን ምክር ለመስማት ምን ያህል ክፍት ነህ?
3. አቤሴሎም የተቀባ ሰው እንደነበረ ከእስራኤል ሰዎች አነጋገር እንረዳለን፤ በአቤሴሎምና በዳዊት ቅባት መካከል ምን ዓይነት ልዩነት ትመለከታለህ? በቁ11-15 ላይ ስደተኛው ዳዊት በካህናቱ በሳዶቅና በአብያታር አማካኝነት ወደ እስራኤል ሽማግሌዎች የላከውን መልዕክት ስታነብ፤ ዳዊት የእስራኤልን ህዝብና፣ አሜሳይ የተባለውን ሰው ልብ ወደራሱ ለመመለስ የተጠቀመባቸው ሁለት ዋና ዋና መንገዶች ምንና ምንድናቸው?
4. በ2ኛ ሳሙ 16፡13 ላይ ዳዊትን የተሳደበውና የተራገመው ሳሚ ዛሬ በ2ኛ ሳሙ 19፡16-23 ላይ ስንመለከት የተለየ ሰው ሆኖ ነው የቀረበው። ዳዊት ያኔ በተሰደበበት ወቅትና ዛሬ በሚገኝበት ሁኔታ መሃል የሚታይህ ትልቁ ልዩነት ምን እንደሆነ ተናገር። ቁ20 ላይ ሳሚ ከዮሴፍ ቤት ለዳዊት ያስታውሰዋል፤ ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋራ ያሳለፈው ነገር በዚህ ሥፍራ ከምናየው በዳዊትና በሳሚ መካከል ከሚካሄደው ነገር ጋራ የሚመሳሰለው በምን መንገድ ነው?
5. 2ኛ ሳሙ 19፡24-30ን በአንድነት አንበቡት። በ2ኛ ሳሙ 16፡3-4 ላይ ሲባ ስለ ሚምፊቦስቴ ከንጉሱ ጋራ አለመምጣት ለዳዊት የነገረውንና፤ በ2ኛ ሳሙ 19፡25-26 ላይ ሚምፊቦስቴ ራሱ ለምን ከዳዊት ጋራ እንዳልሄደ የሰጠውን መልስ ስትመለከት የማናቸውን ንግግር ታምናለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ። በዚህ ሥፍራ አንተ በዳዊት ቦታ ብትሆን የእነዚህን የሁለት ሰዎች አነጋገርና ድርጊታቸውን ሁሉ ከተመለከትክ በኋላ ፍርድህ ከዳዊት ፍርድ ጋራ በምን ይለይ ወይም ይመሳሰል እንደነበረ ተናገር።
6. በቁ31-39 ውስጥ ቤርዜሊ ንጉሱ በሚያስፈልገው ወቅት ምግብን መስጠቱ ከንጉሱ አንዳች ነገርን ለመቀበል በማሰብ እንዳልነበረ የሚጠቁመን ከምንባቡ ውስጥ ምን ሃሳብ ትመለከታለህ? እነዚህን ቁጥሮች በደንብ አተኩረን ስንመለከት፤ ቤርዜሊ ንጉሱን ዳዊትን መመገብ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰዎች እንዲያድጉና ህይወታቸው እንዲሻሻል የሚፈልግ ሰው መሆኑንም ማየት እንችላለን፤ ይህንን እውነት የሚያረጋግጥልን የትኛው ሃሳብ እንደሆነ አስረዳ።
7. ዳዊት በቁ12-13 ላይ እግዚአብሄር በእናንተ ላይ ንጉስ እንድሆን ስለቀባኝ ከሚለው ሃሳብ ይልቅ ህዝቡን ወደ እርሱ የጠራው ምንን በማስታከክ ነበረ? ቁ42ትን ስንመለከት "የይሁዳም ሰዎች ሁሉ ለእስራኤል ሰዎች ይህንን ያደረግነው ንጉሱ የቅርብ ዘመዳችን ስለሆነ ነው" በማለት የይሁዳ ሰዎች የተናገሩት ንግግርና በአጠቃላይ ከቁ40-43 ከእስራኤላውያን ጋራ የተመላለሱበትን ነገር ስናይ፤ ዳዊት የዘራውን እያጨደ ነው ማለት የሚያስችለን ነገር ምንድነው?
8. መለስ ብለን ቁ5-8ትን ስናነብ ኢዮአብ ለንጉሥ ዳዊት ቀጥተኛ በሆነና በማያሻማ ሁኔታ ሃሳቡን መግለጹ ለእርሱም ሆነ ለጠቅላላ ለእስራኤል የጠቀመው በምን መንገድ ነው? አንተስ ወገኖች ማረምና ማስተካከል የሚገባህን ነገር ሲነግሩህ ታኮርፋቸዋለህ ወይስ ለጊዜው ቢያምህም እንኳን እውነቱን ተቀብለህ በተግባር ታውለዋለህ? ለመዋጥ የሚያስቸግረንን እውነት ለመናገር የማይፈሩትን ወገኖች እግዚአብሄር ሲሰጠን፤ እንደተቀናቃኝ በመቁጠር ከአካባቢያችን ለማስወገድ መሞከር ሞኝነት እንደሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል።

# ጥናት ሃያ 2ኛ ሳሙ 20፡1-26

የጥናት ዓላማ፡- ሳቤዔ የህዝቡን ጊዜያዊ ስሜት መጋጋል ተመልክቶ ሁኔታው ሊፈታ የማይችል ቅራኔ አድርጎ በማቅረብ የራሱን የልብ መሻት ማስፈጸሚያ እንዳደረገ ሁሉ፤ በየቤተክርስትያኑም በዚሁ ዓይነት መንፈስ ሕዝብን ለመከፋፈል ወደ ኋላ የማይሉ ሰዎች እንደሚኖሩ ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በዚህ ጊዜ የቤክሪ ልጅ ስሙ ሳቤዔ የተባለ አንድ ምናምንቴ ብንያማዊ በዚያ ነበረ፤ እርሱም መለከት ነፍቶ እንዲህ ሲል ጮኸ፤ እኛ ከዳዊት ድርሻ የለንም፤ ከእሴይም ልጅ ርስት የለንም፤ እስራኤል ሆይ እያንዳንድህ ወደ ድንኳንህ ተመለስ።" 2 ሳሙ 20፡1

1. 2ኛ ሳሙ 20፡1-26 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ላይ ሕዝቡ በሁለት ወገን እንደተከፈለ እንመለከታለን፤ ሁለቱ ወገኖች ማንና ማን ይባላሉ? የእነዚህ ሁለት ወገን መሪዎችስ ማንና ማን ይባላሉ? ዳዊት በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ቤተ መንግሥቱ በተመለሰ ጊዜ ትቷቸው የሄዳቸውን ቁባቶቹን እንዳገኘ ቁ3 ይነግረናል፤ በዳዊት ተመልሶ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣት ለእነዚህ ቁባቶቹ ያገኙትና የተደረገላቸው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር።
2. በቁ3 ላይ የምናያቸው የዳዊት ቁባቶች የነበሩ አሥር ሴቶች የሚገኙበትን ሁኔታ የሚገልጹትን ሃሳቦች በመዘርዘር ተናገር። በአንተ አመለካከት ስታየው፤ እነዚህን አሥር ሴቶች አሁን የሚገኙበት ሁኔታ ውስጥ እንዲገኙ የማገዳቸው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? በእነዚህ ሴቶች ላይ የደረሰው ሁኔታ ለእኛ ምን ሊያስተምረን ይችላል ብለህ ታምናለህ?
3. በአመጽ የተነሳውንና እስራኤል ሁሉ የዳዊትን ንጉስነት እንዳይቀበል ያደረገውን ሳቤዔን ለመውጋር በቁ4-5 ላይ ዳዊት አሜሳይን፣ በቁ6 ላይ ደግሞ አቢሳን ለጦርነት ሲያዘጋጅ እናያለን፤ እስከዛሬ ድረስ የጦር መሪው የነበረው ኢዮአብ ለምንድነው በእነዚህ ሰዎች የተተካው? ቁ4-7ትን ስናነብ አሜሳይ ዳዊት ባዘዘው ቀን ተመልሶ አለመምጣቱ ለሳቤዔና ለተከታዮቹ ሁኔታውን ምቹ ያደረገላቸው በምን መንገድ ነው?
4. ይህ አሜሳይ የተባለው ከቁ4 ጀምሮ በቁ8-10 ላይ ስለምናየው ሰው የምታውቀው ምን ነገር እንዳለ ተናገር። አሜሳይ ስለተባለው ሰው የምናውቀውንና በዚህ በቁ8-13 ውስጥ የተካሄደውን ነገር ስናነብ፤ ኢዮአብ ይህንን ሰው መግደል የሚያስችለው ምን በደል አግኝቶበታል ብለህ ታምናለህ? እነዚህኑ ቁጥሮች ስናነባቸው ኢዮአብ በአሜሳይ ላይ ክፉ ነገር እንደማያደርግበት ለማዘናጋት ከተጠቀመባቸው ነገሮች ብለህ የምትለው አንድ ነገር ምንድነው?
5. ቁ13 ላይ ስናነብ ኢዮአብና ሰራዊቱ በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ወይም ለመግደል የሚያሳድዱት ሰው ማን ነበረ? በቁ14 እና 15 በተለይም ደግሞ ቁ15 ይህንን ሰው ለማግኘት ሲባል የኢዮአብ ሰራዊት የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ?
6. ቁ14 ላይ ቤክሪያውያን ሁሉ ሳቤዔን እንደተከተሉት ስናነብ በቁ15-19 ላይ ግን የዚህን ሰው የስንፍና መንገድ ለመከተል እንቢ ያለ አንድ ሰው እንመለከታለን፤ ይህ ሰው ሁሉ ስለተከተለ ብቻ ለመከተል እንቢ ያለው ሰው ማን ነው? በዚህ ክፍል ከኢዮአብ ጋራ ስትነጋገር የምናያት ሴት ኢዮአብን ለማሳመን በቁ19 ላይ አስተውሎ እንዲያደርግ የዘረዘረችለት ሶስት ሁኔታዎች ምን ምን እንደነበሩ ተናገር።
7. በቁ20-23 መሰረት ይህች ጥበበኛ ሴት የዘረዘረችለት ሃሳቦች ኢዮአብን አመለካከት መቀየር መቻሉን የሚጠቁመን ነገር የትኛው ነው? "ከዚህም በኋላ ብልህነት የተሞላበትን ምክሯን ይዛ ወደ ህዝቡ ሁሉ ሄደች፤ እነርሱም የቢክሪን ልጅ የሳቤዔን ራስ ቆርጠው ለኢዮአብ ወረወሩለት" በማለት ቁ22 ይናገራል። ይህች ሴት የከተማይቱን ሰዎች ለማሳመንና የሳቤዔን ራስ ለማሰጠት ምን የነገረቻቸው ይመስልሃል?
8. በ2ኛ ሳሙ 19፡41-43 ላይ የተከሰተው ሁኔታ በአንድነት ይነበብ። በ2ኛ ሳሙ 20፡1 ላይ ተመልሰን ስንመለከት ምናምንቴ በመባል የተጠራው የቢክሪ ልጅ ሳቤዔ ለወሰደው እርምጃ በር የከፈተለት ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ የራሳቸውን የልብ ምኞች ለመፈጸም ህዝብን ለመከፋፈል ወደ ኋላ የማይሉ ሰዎች እንደሚኖሩ ትረዳለህ ወይ? በዘመናችንም በሳቤዔ መንፈስ የእግዚአብሄርን ህዝብ ለመክፈል የማይገዳቸው ሰዎች እንደሚኖሩ ማወቅና መጠንቀቅ ያስፈልገናል።

# ጥናት ሃያ አንድ 2ኛ ሳሙ 21፡1-22

የጥናት ዓላማ፡- ምንም እንኳን ለገባዖናውያን የተገባው ቃል ኪዳን ዘመናት ቢያልፉትም፤ በቃል ኪዳኑ መፍረስ እግዚአብሄር እንደተቆጣ ሁሉ፤ በዛሬም ዘመን ቢሆን እግዚአብሄር አምላክ ስላልተለወጠና ቃሉን የማያጥፍ አምላክ ስላልሆነ፤ እኛም የገባንወን የትዳርም ሆነ ሌላ ቃል ኪዳኖች እንድንጠብቅ እንደሚፈልግ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡-"በዳዊት ዘመነ መንግሥት፣ በተከታታይ ለሶስት ዓመት ረሃብ ሆነ፤ ስለዚህ ዳዊት እግዚአብሄርን ጠየቀ፤ እግዚአብሄርም ሳዖል ገባዖናውያንን ስለ ገደለ እርሱና ቤቱ የደም ዕዳ አለባቸው አለ።" 2ኛ ሳሙ 21፡1

1. 2ኛ ሳሙ 21፡1-22 በአንድነት ይነበብ። በቁ 1-2 ላይ ስናነብ ንጉሥ ሳዖል በእስራኤል ላይ ንጉሥ በነበረበት ወቅት ያጠፋውን ጥፋት እግዚአብሄር በዳዊት ዘመነ መንግሥት ለማረም ሲሞክር እናያለን፤ ሳዖል ራሱ በነበረበት ጊዜ ከማድረግ ይልቅ በዳዊት ጊዜ ማድረግ የፈለገው ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? ሳዖል በገባዖን ሰዎች ላይ ይህንን ለማድረግ ስላነሳሳው ሁኔታ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ምን የምንመለከተው ነገር አለ?
2. ቁ1-6ት ውስጥ ስናነብ፤ ዳዊት እግዚአብሄር የረሃቡን ምክንያት ካስታወቀው በኋላ እግዚአብሄር ደስ ያልተሰኘበትንና ያዘነበትን ነገር ለማስተካከል ሲሞክር ይታያል፤ በመጀመሪያ ደረጃ ዳዊት የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ዳዊት ከገባዖናውያን ጋራ ድርድር ሲያደርግ ከእርሱ ሊያገኙ ወይም እነርሱ እንዲያደርጉት የሚጠይቃቸው ነገር ምን ትመለከታለህ? ዳዊት በቁ3 ላይ "የእግዚአብሄርን ርስት ትባርኩ ዘንድ" ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. ንጉሥ ዳዊት የእግዚአብሄርን ሃሳብ ለመፈጸም ቁ5-9ኝን ስናነብ ገባዖናውያን የጠየቁት ከባድ ጥያቄ ቢሆንም ሁኔታውን ለማስተካከል የሚያስከፍለውን ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ እንደሆነ ይታያል፤ የገባዖን ሰዎች ነገሩ እንዲስተካከል ካስፈለገ ብለው ከዳዊት የጠየቁት ምን እንዲያደርግ ነበረ? በቁ7 ላይ ዳዊት ይህንን ስህተት ለማስተካከል ሲሞክር ሌላ ተጨማሪ ስህተት እንዳይፈጸም ጥንቃቄ ሲያደርግ የምንመለከተው እንዴት ነው?
4. በቁ8 ላይ ስንመለከት እንዲገደሉ አልፈው የተሰጡት አራቱ ወንዶች፤ የኢዮሔል ልጅ የርጽፋ እና የሳዖል ልጅ የሜሮብ ልጆች እንደነበሩ እናነባለን። እነዚህ ሰባት ልጆችና ሁለቱ እናቶች በገባዖን ሰዎች ላይ የፈጸሙት ሐጥያት ምን ነበረ? የኢዮሔል ልጅ ርጽፋ ለልጆችዋ የነበራትን ፍቅር የገለጸችበት መንገድ ምን ነበረ? ይህች ሴት ለልጆችዋ ያደረገችው ነገር ነፍሳቸውን ባይመልስም እንኳን ምን ያተረፈላቸው ነገር ትመለከታለህ?
5. አንተ በዳዊት ሥፍራ ብትሆንና እግዚአብሄር ያዘነበት ነገር ምን እንደሆነ ገልጾ ቢነግርህ፣ የገባዖን ሰዎች ደግሞ ዳዊትን እንደጠየቁት ዓይነት ጥያቄ ቢጠይቁህ የምትቸገርበት አንድ ነገር ምንድነው ትላለህ? ቁ14 ላይ "ከዚያ በኋላም ስለምድሪቱ የቀረበውን ጸሎት እግዚአብሄር ሰማ" በማለት ይናገራል። "ከዚያም" የሚለው ሃሳብ ሊጠቁመን የሚፈልገውና ጸሐፊው እንድናየው የፈለገው እውነት ምንድነው? በሐጥያት እና በጸሎት መልስ መካከል ሊኖር ስለሚችለው ግንኙነት ከዚህ ክፍል ምን መማር እንችላለን?
6. ዳዊት ሃይለኛ ጦረኛ እንደነበረ የተለያዩ ሰዎች ሲመሰክሩለት እናውቃለን፤ አሁን በዚህ በቁ15-17 ላይ ዳዊት ራሱን መከላከል አቅቶት ከራፋይም ዘር የሆነው ሰው ሊገድለው የነበረው በምን ሁኔታ ስላገኘው ነው ትላለህ? ዳዊት በድካም በነበረበት በዚህ ጊዜ በፍልስጤማዊው ሰው ሰይፍ እንዳይሞት የታደገው ሰው ማን ነበረ? ዳዊት የድካም ጊዜ እንደነበረው ሁሉ እኛም አንድ ቀን መድከም ስለሚኖር ከጠላት የሚታደጉን ወገኖች ከጎናችን እንደሚያስፈልጉን አምነን መቀበል ይኖርብናል።
7. በቁ15-22 ላይ በሚገኙት ስምንት ቁጥሮች ውስጥ የእስራኤል ጠላት ስንት ጊዜ ለጦርነት ሲመጣባቸው ነው የምናየው? ጠላት አንዴ ተሸንፍኩ ብሎ እንደማይተውህ ልትረዳ ያስፈልግሃል።
8. ቁ1ድን መለስ ብለን ስንመለከት፤ ሳዖል በህይወቱ በጣም ብዙ ዓይነት ሰዎችን እንደገደለ እናውቃለን፤ ታዲያ በዚህ ክፍል ውስጥ በተለይ ቁ1 ላይ ሳዖል ገባዖናውያንን መግደሉን እግዚአብሄር እንደ ትልቅ ወንጀል አድርጎ የወሰደበት ምክንያት ለምንድነው? በአንተ ህይወት ውስጥ የገባኸውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ምን ያህል ትተጋለህ? እግዚአብሄር የቃል ኪዳን አምላክ ስለሆነና የገባውን ቃል ለመፈጸም ስለሚተጋ፤ ምንም ያህል የሚያስከፍል ቢሆን የእርሱ ልጆች የሆኑ ሁሉ የቃል ኪዳን ጠባቂዎች እንዲሆኑ ይፈልጋል።

# ጥናት ሃያ ሁለት 2ኛ ሳሙ 22፡1-51

የጥናት ዓላማ፡- ዳዊት ክፉ ቀናት እንዳሳለፈ ሳይክድ፤ ነገር ግን ከነዚያ ሁሉ ያዳነውን እግዚአብሄርን ለማመስገን እንደወሰነ ሁሉ፤ እኛም በህይወታችን ያሳለፍናቸውን የመከራ ቀናት በመዘርዘር ዘመናችንን ከምንጨርስ ይልቅ፤ ከመከራዎቻችን ሁሉ የታደገንን እግዚአብሄርን በማመስገን ላይ ማተኮር የተሻለ እንደሚሆን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እግዚአብሄር ከጠላቶቹ ሁሉና ከሳዖልም እጅ በታደገው ጊዜ፤ ዳዊት የዚህን መዝሙር ቃል ለእግዚአብሄር ዘመረ፤ እንዲህም አለ" 2ኛ ሳሙ 22፡1

1. 2ኛ ሳሙ 22፡1-51 በአንድነት ይነበብ። በአጠቃላይ ምዕራፍ 22ትን ስናነብ፤ በተለይም ደግሞ ቁ1 ላይ ዳዊት በጠላቶቹ ላይ ያገኘውን ድልና፣ ያመለጠውን ማምለጥ በሙሉ የማን እጅና የማን ድል አድርጎ ነው ሲያቀርብ የምናየው? የዳዊትን ህይወት መለስ ብለን ስንመለከት፤ ሳዖል ሊገለው ሲመጣበት በዋሻ ውስጥ በመደበቅ፣ ሳዖል ሊያገኘው ሲመጣ ወደ ፍልስጤም ምድር የሸሸውና የመሳሰሉትን በማድረግ ማምለጡን እያወቀ ለምንድነው ድሉን የራሱ አድርጎ የማይናገረው?
2. በቁ1-3 ውስጥ ብቻ እንኳን ስናነብ ዳዊት እግዚአብሄር ለእርሱ ማን እንደሆነ የገለጸባቸውን ሃሳቦች ሁሉ ተናገር። በቁ5-7 ላይ ዳዊት የሚናገረውን ስንመለከት በህይወቱ ያለፈባቸውን አስከፊ ሁኔታዎች ጠቅለል አድርጎ አስፍሯቸው እናገኛለን። ዳዊት ገጥመውኛል የሚላቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ምን ምንድናቸው? እነዚህን በመሳሰሉ አስከፊና ከባድ በሆኑ ነገሮች ውስጥ በገባ ጊዜ ዳዊት ለራሱ መፍትሄ አድርጎ የወሰደው ነገር ምን ነበረ? አንተስ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ስትገባ መፍትሄ አድርገህ የምትወስደው ምንድነው?
3. ዳዊት እግዚአብሄርን እንደመፍትሄው አድርጎ ወደ እርሱ እንደጮኸ ተመልክተናል፤ የዚህ ሰው ጩኸት ከእግዚአብሄር ዘንድ መልስ እንዳመጣለት የሚጠቁመን ከቁ7-20 ባሉት ውስጥ የትኛው ጥቅስ ነው ትላለህ? "ከብርቱ ጠላቶቼ፤ ከማልቋቋማቸው ባልጋሮቼ ታደገኝ" በማለት ንጉሥ ዳዊት በቁ18 የሚናገረውን ስታነብ፤ ይህንን ሲል ዳዊት በአዕምሮው የትኛውን ጠላት ወይም ደግሞ የትኛውን ባለጋራ እያሰበ የሚናገር ይመስልሃል?
4. ዳዊት ከቁ21-27 ላይ ከጠላቶቹ ጋራ ባሳለፋቸው ጊዜያት ውስጥ በህይወቱ የታዩትን ነገሮች በተለያየ መንገድ ሲዘረዝር እንመለከታለን፤ ለምሳሌ ያህል ቁ23ትን ብንወስድ "ሕጉ ሁሉ በፊቴ ነው፤ ከሥርዓቱም ዘወር አላልኩም" የሚለው አነጋገር በህይወቱ መቼ ሲፈጸም አይተሃል? እግዚአብሄር ለዳዊት ምኑ እንደሆነለት በቁ3 ላይ ከሚናገረው በተጨማሪ፤ በቁ29 እግዚአብሄር ለእርሱ ምኑ እንደሆነለት ነው የሚናገረው? ለአንተስ እግዚአብሄር የጨለመ ሁኔታ ውስጥ በገባህበት ወቅት እግዚአብሄር ብርሃን ሆኖልህ ያውቃል ወይ?
5. ምዕራፍ 22ትን በአጠቃላይ ስንመለከት እግዚአብሄር ለዳዊት ያደረገውንና የሆነለትን ነገር በሥፋት ሲዘረዝር እንመለከታለን፤ ቁ29-31 ላይ ስናነብ የእግዚአብሄር ማዳንና እርዳታው ለዳዊት ብቻ እንዳልሆነ የሚያስገነዝበን ጥቅስ የትኛው ነው? ቁ32-37 በሰፈረው ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር በዳዊት ህይወት እንዳደረገ ወይም እንደሚያደርግ የተነገሩትን ነገሮች ዘርዝር።
6. በቁ44 ላይ ስናነብ "ከህዝቤ ከተቃጣብኝ አደጋ አዳንከኝ" ይላል። ዳዊት በዚህ ቁጥር ላይ የሚናገረው ማንን ወይም ደግሞ እነማንን አስመልክቶ ነው ብለህ ታምናለህ?
7. ቁ51 ላይ ዳዊት የሚናገረውን በማንበብ እግዚአብሄር ለእርሱ የገባለትን የቃል ኪዳን ከልቡ አምኖ እንደተቀበለ የሚያረጋግጥልን በምን መንገድ ነው?
8. በዳዊት ሕይወት ውስጥ በጣም ብዙ የሆኑ ውጣ ውረዶችን እንዲሁም መልካም ሁኔታዎችን እንዳሳለፈ እናውቃለን፤ ሆኖም ዳዊት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ወደኋላ ዘወር ብሎ ህይወቱን ሲመዝን ለአይኑ ጎልቶ የታየው የትኛው ሁኔታ ነው? አንተስ ህይወትህን ስትመዝነው ጎልቶ የሚታይህ መከራህ ይሆን ወይስ በመከራህ የደረሰልህ እግዚአብሄር? በህይወታችን ባሳለፍናቸው መከራዎችና ችግሮች ላይ ከማተኮር ይልቅ፤ በመከራችን ሰዓት የደረሰልንን እግዚአብሄር እያሰብን አመስጋኞች ልንሆን ይገባናል።

# ጥናት ሃያ ሶስት 2ኛ ሳሙ 23፡1-39

የጥናት ዓላማ፡- በማናቸውም ቦታ ላይ የእግዚአብሄርን ህዝብ የሚገዙና የሚያስተዳድሩ ቅዱሳን፤ እግዚአብሄር በዳዊት በኩል ያስተላለፋቸውን፤ እነዚህን ሁለት መመሪያዎች ማለትም፤ በጽድቅ መግዛትና፣ በፈሪሃ እግዚአብሄር ማስተዳደርን ዋነኛ የህይወት መመሪያ በማድረግ ሕዝቡን ሊመሩ እንደሚገባቸው ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሰዎችን በጽድቅ የሚገዛ፤ በፈሪሃ እግዚአብሄርም የሚያስተዳድር፤ እርሱ ደመና በሌለበት፤ በማለዳ ፀሐይ በምትወጣበት ጊዜ እንዳለው ብርሃን ነው።" 2ኛ ሳሙ 23:3-4

1. 2ኛ ሳሙ 23፡1-39 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ ዳዊት ስለራሱ ማንነት የሚዘረዝራቸው አራቱ ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ዳዊት በተለይም በአራተኛ ደረጃ የተናገረውን ነገር ስንመለከት ይህ ሰው ምንም እንኳን በእግዚአብሄርና በሰዎች ዘንድ የከበረ ሥፍራ እንደተሰጠው ቢናገርም፤ የተነሳበትንና ማንነቱን የረሳ ሰው እንዳልሆነ የሚያስገነዝበን ሃሳብ ምን እንደሆነ ተናገር። አንተስ እግዚአብሄር ከየት አንስቶ የት እንዳደረሰህ ዘወትር ታስታውሳለህ ወይ?
2. ቁ1-4 ላይ ያለውን ሃሳብ ስታነብ ዳዊት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚያስተላልፈውን መልዕክት በቀጥታ ከእግዚአብሄር ለመግለጽ የተጠቀመባቸውን ቢያንስ አምስት ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ስንመለከት እግዚአብሄር በዳዊት አንደበት ውስጥ፤ ሰዎችን በጽድቅ የሚገዛንና፤ በፈሪሃ እግዚአብሄር የሚያስተዳድርን ሰው ከሁለት ነገሮች ጋራ ሲያመሳስለው እንመለከታለን፤ እነዚህ ከጽድቅ አገዛዝና ከፈሪሃ እግዚአብሄር አስተዳደር ጋራ የተመሳሰሉት ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
3. ቁ9 እና 10 ላይ የምናየው የአሆሃዊው የዱዲ ልጅ የኤልዔዘር የጀግንነት ታሪክ ስታነብ፤ ሌላ ከዚህ ጋራ የሚቀራረብ ሁኔታን ያሳለፈ ሰው ማንን ያስታውስሃል? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስናነብ የዚህን ሰው የልብ ቆራጥነትና ጀግንነቱ ሊደነቅ የሚገባው እንደሆነ ማንም ሊክደው የማይችል እውነት ነው፤ ሆኖም ግን ጸሐፊው በዚህ ክፍል ውስጥ ለተካሄደው ነገር ሁሉ የድሉ ባለቤትና የድል ሰጪው ማን እንደሆነ አድርጎ ነው የሚያቀርብልን?
4. በቁ9-10 ላይ በተመለከትነው በአሆሃዊው የዱዲ ልጅ የኤልዔዘር ታሪክ ውስጥና፤ በቁ11-12 ውስጥ በምናነበው በአሮዳዊው በአጌ ልጅ በሣማ ታሪክ መሃል የምታያቸው ተመሳሳይነቶች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር አስረዳ። በእነዚህ ሁለት ታሪኮች ውስጥ ከምንመለከተው አንዳንዶች ለእግዚአብሄር ህዝብና ለአገራቸው ቀጥ ብለው ሲቆሙ፤ አብዛኛው ህዝብ ሲያደርግ የምናገኘው ነገር ምንድነው?
5. ቁ13-17 ላይ የምናነበው ታሪክ የተከናወነበትን ጊዜ በግምት ለመናገር የሚያስችለንና ወቅቱን የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው እንደሆነ ተናገር። በቁ15 ላይ ዳዊት "በቤትልሔም በር አጠገብ ካለችው ጉድጓድ ውሃ ማን ባመጣልኝ? አለ" የሚለውን ሃሳብ ስትመለከት፤ ዳዊት በነበረበት አካባቢ ምንም ዓይነት ሊጠጣው የሚችለው ውሃ ስላልነበረ ነው ወይስ ለምን ይመስልሃል ዳዊት በቤትልሄም በር አጠገብ ካለችው ጉድጓድ ውሃ መጠጣት የተመኘው?
6. በቁ20-23 ላይ የምናነበው የዮዳሄ ልጅ በናያስ ታሪክ ወደ አዕምሮህ የሚያመጣው ምን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንዳለ ተናገር።
7. ቁ3ትን መለስ ብለን ስንመለከት፤ እግዚአብሄር ደስ የሚሰኝበትና እርሱ የሚከብርበት ዓይነት አገዛዝና አስተዳደር መለያው ምን እንደሆነ ነው ዳዊት የሚናገረው? በቤተ ክርስትያን አካባቢ የምታያቸው መሪዎችና አስተዳዳሪዎች ምን ያህል እነዚህን ሁለት መርሆዎች የሚከተሉ ናቸው? የእግዚአብሄርን ህዝብ የሚገዙና የሚያስተዳድሩ ቅዱሳን፤ እግዚአብሄር በዳዊት በኩል ያስተላለፋቸውን፤ በጽድቅ መግዛትና፣ በፈሪሃ እግዚአብሄር ማስተዳደርን ዋነኛ መመሪያቸው ሊያደርጉት ይገባል።

<u>ጥናት ሃያ አራት 2ኛ ሳሙ 24፡1-25</u>

የጥናት ዓላማ፡- ንጉስ ስለሆነ ዳዊት ከኢዮአብ ምክር ለመስማት እንቢተኛ መሆኑ ለብዙዎች ህይወት መጥፋት እንደሆነ ሁሉ፤ በዚህም ዘመን እግዚአብሄር በቤተ ክርስትያን ውስጥ በህዝቡ ላይ የሾማቸው ሰዎች ታናናሽ አድርገው ከሚያዩአቸው ቅዱሳን ምክርን ላለመስማት ሲወስኑ መጨረሻው ለመልካም እንደማይሆን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ኢዮአብ ግን ንጉሱን…ንጉሱ ጌታዬ ግን ይህንን ለማድረግ የፈለገው ለምንድነው? ሲል መለሰለት፡፡ ሆኖም የንጉሱ ቃል ኢዮአብንና የሰራዊቱን አዛዦች ስላሸነፋቸው የእስራኤልን ሰራዊት ለመመዝገብ ከፊቱ ወጥተው ሄዱ።" 2 ሳሙ 24፡3-4

1. 2ኛ ሳሙ 24፡1-25 በአንድነት ይነበብ። በ2ኛ ሳሙ ምዕራፍ 24 ውስጥ እና በ1ኛ ዜና ምዕራፍ 21 ላይ የሰፈሩት ታሪኮች በሁለት ቦታ የሰፈሩ ነገር ግን ሁለቱም በአንድ ወቅት የሆነን ታሪክ የሚናገሩ ናቸው። በ2ኛ ሳሙ 24፡1 እና በ1ኛ ዜና 21፡1-2 ላይ ስንመለከት ዳዊት ህዝቡን እንዲቆጥር እግዚአብሄር እንዳነሳሳው አድርጎ ሲናገር፣ በሌላው ክፍል ደግሞ ሰይጣን የዳዊትን ልብ እንዳነሳሳ እናነባለን፤ እነዚህ ቅራኔ የሚመስሉ ሃሳቦች በምን መንገድ ነው ማስታረቅ የሚቻለው ትላለህ?
2. በቁ2-3 ውስጥ ስናነብ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ ያሉት የእስራኤል ነገዶች ሁሉ በቶሎ ይቆጠሩ ዘንድ ከንጉሱ ትዕዛዝ የተቀበሉት እነማን ነበሩ? ይህ ሕዝብን የመቁጠር ትዕዛዝ ከንጉሥ ዳዊት ዘንድ ሲነገራቸው፤ እነዚህ መልዕክቱን የተቀበሉት ሰዎች በተለይም ደግሞ ኢዮአብ ትዕዛዙን በምን ዓይነት መንገድ የተቀበለው ይመስልሃል? ኢዮአብ ዳዊት የዚህ ዓይነቱን ነገር ማድረግ የማይገባና መልካም እንዳልሆነ ንጉሱን ሊመክረው ሲሞክር የሆነው ነገር ምን ነበረ?
3. ከቁ5-9 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ዳዊት እግዚአብሄርን ደስ የማያሰኝ ነገር ከማድረጉ ባሻገር፤ በተጨማሪ አገራቱን የሚጎዳ ያስከተለው ምን ነገር ትመለከታለህ? ቁ10ርን ስናነብ የዳዊትን መንፈሳዊ ሕይወት ከብዙ ሰዎች መንፈሳዊ ህይወት የሚለየው አንድ ነገር መመልከት እንችላለን፤ ይህ ዳዊትን ከከብዙዎች የሚለየው ነገር ምንድነው?
4. ዳዊትን በቁ10 ላይ ስናየው ማንም ሰው ሃጥያቱን ሳይነግረው በራሱ ጥፋቱን አውቆ በእግዚአብሄር ፊት ንስሃ ሲገባ ይታያል፤ ታዲያ ለምንድነው ንስሃ ከገባ በኋላ በቁ11-13 ውስጥ በነብዩ በኩል ቅጣት እንደሚያገኘው የተነገረው? እነዚህንው ቁጥሮች ቀረብ ብለት በትኩረት ስንመረምራቸው የእግዚአብሄርን ጸጋና መልካምነቱንም የሚጠቁመን ሃሳብ አላቸው፤ የእርሱን ጸጋ ማየት የምንችልበት ሃሳብ የትኛው ነው ትላለህ?
5. በቁ14 ላይ ዳዊት ለጋድ "እጅግ ተጨንቄአለሁ" በማለት ይናገራል፤ ምንድነው ዳዊትን በዚህ ጊዜ ያስጨነቀው ትላለህ? ንጉሱ ዳዊት በቁ14 ላይ ነብዩ ጋድ ምርጫውን አስመልክቶ ሲነግረው "ምህረቱ ታላቅ ስለሆነ በእግዚአብሄር እጅ እንውደቅ፤ በሰው እጅ ግን አልውደቅ" በማለት ነግሮት እንደነበረ እናያለን፤ ቁ14-16ትን ስናነብ ዳዊት ስለ እግዚአብሄር ባህርይ የተናገረው ነገር እውነትነቱ ሲረጋገጥ የምንመለከተው እንዴት ነው? አንተስ የእግዚአብሄርን ባህርይ ምን ያህል ተረድተሃል?
6. በቁ17 ላይ ዳዊት ራሱን የአባቱን ቤት በአንድ በኩል፤ የእስራኤልን ሕዝብ ደግሞ በሌላ በኩል አቁሞ፤ ቅጣት የሚገባው ለማን እንደሆነ ነው ለእግዚአብሄር ሲናገር የምንሰማው? መቀጣት አይገባውም ብሎ ከእግዚአብሄር ጋራ ሲሟገት የምንመለከተው ማንን አስመልክቶ ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ 10፡11 ላይ የተናገረው እውነት በዚህ ክፍል ዳዊት በወሰደው እርምጃ ተከስቶ የሚታየው በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ። አንተስ ስለ ሃጥያትህ በሰዎች ታሳብባለህ ወይስ ለሃጥያትህ ሃላፊነቱን ትወስዳለህ?
7. ቁ18-25 ላይ ያለውን ታሪክ ስናነብ ኦርና ለመሰዊያ የሚሆነውን ዓውድማውን ለዳዊት በነጻ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ ሳለ፤ ለምንድነው ዳዊት ከኦርና እጅ ዓውድማውን በነጻ ለመውሰድ ፈቃደኛ ያልሆነው?
8. በቁ3-4 ላይ ተመልሰን ስንመለከት ዳዊት ካመጣው ሃሳብና ኢዮአብ ካመጣው ሃሳብ የማንኛቸው ሃሳብ ትክክል ነበረ ብለህ ታምናለህ? በሰው እይታ ስንመለከተው ታዲያ ለምን የዳዊት ሃሳብ ተፈጻሚ እንዲሆን ተደረገ? በቤተ ክርስትያን ውስጥ ስልጣን የያዘ፤ ነገር ግን ከቅዱሳን ምክርን መስማት እንደማያስፈልገው የሚያምን ሰው ገጥሞህ ያውቃል ወይ? በስልጣን ላይ መሆን ማለት ሁሉን ነገር ጠንቅቀን አውቀናል ማለት ስላልሆነ፤ እግዚአብሄር በቅዱሳን ውስጥ የሚመክረንን ምክር መስማት ጥበብ ነው።